# መመሪያ ቁጥር 1071/2017

## የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ስርአት መመሪያ

# DIRECTIVE NO. 1071/2025

## DIRECTIVE ON EXCISE TAX MANGEMENT SYSTEM

ግንቦት፣ 2017 ዓ.ም

**May/ 2025**


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

# መመሪያ ቁጥር. 1071/2017

# የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ስርአት መመሪያ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን በትክክል ለማስፈጸም፤ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች በማምረት እና በማከፋፈል ሂደት የሚደረገውን የቁጥጥር፤ የክትትል እና የመለየት ስራ ለማገዝ የሚያስችል የኤክሳይዝ ታክስ አስተደደር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2011 አንቀጽ 42(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 1071/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የጥቅሎች ማሸጊያ"** ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የለጠላ መያዥያዎች የሚይዝ ማሸጊያ ነው።
2) **"የተፈቀደለት አከናዋኝ"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ንግድ ስራ ለማከወን በኤክሳይዝ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ፈቃድ የተሰጠው አልኮል የማጣራት፤ የአምራችነት ፈቃድ ያለው የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን፤ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማራን ይጨምራል።
3) **"ስልጣን የተሰጠው ሰራተኛ"** ማለት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ተግባራት እንዲያከናውን በገቢዎች ሚኒስቴር

# DIRECTIVE NO. 1071/2025

# DIRECTIVE ON EXCISE TAX MANGEMENT SYSTEM

WHEREAS, it has become necessary to develop an Excise Tax Management System which facilitates enforcement of excise tax laws, brings transparency and accountability as well as which helps in the control and tracking and tracing of the production and distribution of excisable goods;

NOW THEREFORE, the Ministry of Finance in accordance with the powers vested in it by Articles 29 and 43 of the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 have issued this Directive.

## SECTION I

## GENERAL PROVISIONS

### 1. SHORT TITLE

This Directive may be cited as the "Excise Tax Management System Directive No. 1071/2025 "

### 2. DEFINITIONS

Unless the context otherwise reuires, in this Directive:

1) **"Aggregated packaging"** means any packaging containing more than one unit packet of excisable products;
2) **"Licensed Operator"** means a person licensed under the Excise Tax Proclamation as a Licensed Distiller, Licensed Manufacturer, , which is a natural or legal person who is involved in the trade of excisable products, and shall include a Dealer in Excise Goods.
3) **"Authorised officer"** means a person authorised by the Minister of Revenue or any duly authorized representative thereof



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ወይም ውክልና በተሰጠው ማናቸውም ሰው ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው።

4) "**ለመጠጥነት ዝግጁ የሆነ አልኮል**" ማለት ለመጠጣት በሚያስችል አኳኋን የተዘጋጀ እና ለችርቻሮ ንግድ የሚውል አልኮል ነው።

5) "**የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች/አገልግሎቶች አቅራቢ**" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች/አገልግሎቶች የሚያመርት፣ ለሽያጭ ለማዋል የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

6) "**የቀረጥ ነጻ መደብር**" ማለት የተለዩ እቃዎችን በህግ በተፈቀደው መሰረት ለመንገደኞች የሚሸጥ መደብር ነው።

7) "**አከፋፋይ**" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ አስመጪ ወይም አምራች በመግዛት ለጅምላ ሻጮች ወም ቸርቻሪዎች የሚሸጥ ሰው ነው፤

8) "**የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ**" ማለት ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ የተዘረዘሩት እቃዎች ናቸው።

9) "**የኤክሳይዝ ምልክት**" በኤክሳይዝ ታክስ ምልክት መመሪያ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

10) "**የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ**" ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ለታክሱ ባለሥልጣን የሚከፈልበት ጊዜ ነው፡፡

11) "**የስራ ቦታ**" ማለት የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የሚመረቱበት ፤ የሚከማቹበት ወይም ለገበያ የሚቀርቡበት ሲሆን፤ "የተፈቀደለት ቅጥር ግቢ" ማለት አይደለም"

12) "**የመሸጫ ዋጋ**" ማለት በማናቸውም ሕግ መሰረት የሚከፈልን ታክስ ሳይጨምር የፋብሪካ፤ የወርክሾፕ፤የንግድ ስራ ቦታ ወይም ማእከል የመሸጫ ዋጋ ነው።

13) "**ቅጽ**" ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፤ አግባበነት ባለው መመሪያ ወይም በታክስ አስተ ዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የታዘዘ ቅጽ ነው።

14) "**ሙሉ የስራ ቀን**" የህዝብ በአል፤ የሳምንት የእረፍት ቀን፤ ወይም ግማሽ የስራ ቀን ያልሆነ ቀን ነው።

15) "**ግማሽ የስራ ቀን**" ከሳምንት የእረፍት ቀን በፊት ያለው ቀን ነው።

16) "**የመድረሻ ቦታ ዋጋ**" ማለት በጉምሩክ አዋጅ መሰረት የተተመነ ወደአገር የሚገባ የተለየ እቃ ዋጋ ፤ በዚህ እቃ ላይ የተሰላ የጉምሩክ ቀረጥ እና የማራገፊያ ወጪ ነው።

17) "**የተፈቀደለት አስመጪ**" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች በአስመጪነት የተመዘገበ ሰው ነው።

to perform any function under this Directive;

4) **"Compounded spirit"** means a spirit that is ready for consumption as a beverage and put up for retail sale;

5) **"Dealer in Excise Goods and/or Services"** means a dealer in excise goods and/or services is a person or company who is in the business of producing, buying and/or selling excise goods;

6) **"Duty free shop"** is a shop which sells special goods to the travellers under prescribed provisions.

7) **"Distributor"** shall mean a person that buys excisable goods from one or more Importers or Manufacturers and then sells them to Wholesalers and/or Retailers.

8) **"Excisable Goods"** means goods contained in the schedule attached to the Excise Tax Proclamation.

9) **"Excise Markings"** shall have the same meaning as that provided at Excise Markings Directive.

10) **"Excise Tax Point"** means the time when the excise tax becomes accountable to the Tax Authority.

11) **'Facility'** means any location, building or vending machine where excisable products are manufactured, stored or placed on the market but is not equivalent to "Licensed Premises";

12) **"Selling price"** means the selling price of factory, workshop, business department/centre which does not include tax under any law.

13) **"Form"** means any form prescribed in the Excise Proclamation and relevant Directives, and the Tax Administration Proclamation No. 983/2016.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

18) **"የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ"** ማለት የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርትበት እና የሚያከማችበት ፈቃድ የተሰጠው ቅጥር ግቢ ነው፡፡

19) **"የተፈቀደለት ሰው"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት ሰው ነው፡፡

20) **"የአስተዳደር ስርአት"** የምርት የሂሳብ አያያዝ ስርአት እና ተመሳሳይ ሶፍት ዌር እና ሀርድ ዌርን ጨምሮ የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የአስተዳደር ስርአት ሲሆን፤ የኤክሳይዝ አስተደደርን ስራ ላይ ለማዋል ጥቅም ላይ የሚውለውን የመለየት እና የመከታተል ስርአት ማስፈጸም የሚያስችለውን የኤክሳይዝ ምልክት ስርአት ያካትታል።

21) **"ማምረት"** ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 2(21) የተመለከተውን ጨምሮ በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ወይም በሌላ ፋብሪካ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ መንገድ ምርት የሚመረትበት ማናቸውም ሂደት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

ሀ) የአልኮል መጠቶችን፤ ቢራ እና የወይን ጠጅ ማብላላት፤ ማጣራት፤ መቀላቀል ወይም ለሰው መጠጥነት አገልግሎት ላይ እንዳይውል ማድረግ፤

ለ) የትምባሆ ምርቶችን በሚመለከት ከትምባሆ ቅጠል ጀምሮ፤በሚጨስ፤በሚሸተት፤በሚሳብ በሚታኘክ መንገድ ለፍጆታ እስከሚውልበት ደረጃ ድረስ እንዲሁም የሚጨስ ትምባሆ፤ ሲጋር፤ ሲጋሬት እና ተመሳሰይ ምርቶችን ማምረት፤

ሐ) ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሚመለከት መለየት፤በጅ ወይም በመሳሪያ ወደሌላ ምርት መለወጥ፤ወይም ጥራቱን፤ባህሪውን፤ቅርጹን፤ ውህደቱን መቀየር ወይም የተለያዩ ክፍሎችን መገጣጠም፤

22) **"የገበያ ዋጋ"** ማለት በሻጩ ወይም በገዢው በስሌት የሚደረስበት ሳይሆን በፍላጎት እና በአቅርቦት መካከል ባለው መጣጣም ምክንያት የሚወሰን ወይም የችርጫሮ መሸፃ ዋጋውን ማወቅ ወይም መገመት በማይቻልበት ጊዜ በተወሰነ ዘዴ ስሌት በማከናውን የሚደረስብት ነው።

23) **"ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር"** ማለት የተፈቀደለት ሰው ለታክሱ ባለሥልጣን የሚያቀርበው በሚቀጥለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያመርታቸው ዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር ሲሆን፣ በፋብሪካው ተመርተው ለዚሁ ፋብሪካ በግብዓትነት የዋሉ ጥሬዕቃዎችን ዋጋ ይጨምራል፡፡

24) **"ወደ አገር የሚገባበት ቦታ"** በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች

14) **"Full working day"** means any day which is not a public holiday, a weekly rest day or a half working day;

15) **"Half working day"** means the day immediately preceding the weekly rest day;

16) **"Landed value"** means the aggregate of the value of the imported specific goods accessed under the Customs Proclamation, the custom duty levied thereon and unloading expenses.

17) **"Licensed Importer"** means a person registered as an importer by the Tax Authority to import excisable goods specified under this Directive;

18) **"Licensed Factory Premises"** means a place where Excisable Goods are produced in Ethiopia by a Licensed Manufacturer.

19) **"Licensed Manufacturer"** means a Manufacturer of excise goods in Ethiopia who has obtained the relevant Excise Licence. Further, in addition to the definition at Art. 2(20) of the Excise Tax Proclamation and this Directive, a person who produces excisable goods in their own licensed premises or outsources the manufacture of products to another Licensed Manufacturer.

20) **"Management System"** means the Excisable Goods Management System including its production accounting system, and related software and hardware and includes the Excise Markings system to implement a track and trace approach for excise administration.

21) **"Manufacture"** shall mean, in addition to the definition at Art. 2(21) of the Excise Tax Proclamation, every process, whether natural or artificial, by which goods are



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ወደኢትዮጵያ የሚገቡበት ወደብ፣ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም ድንበር ነው፡፡

25) **"የሕዝብ በአል"** ማለት በኢትዩጵያ ህግ የተወሰነ የህዝብ በአል ነው።

26) **"ቸርቻሪ"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በጥሬ ገንዘብ ወይም በዱቤ ወይም በአደራ ወይም በቅድሚያ ሽያጭ ስርአት በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

27) **"ሽያጭ"** ማለት የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በጥሬገንዘብ ወይም በዱቤ ወይም በአደራ ወይም በቅድሚያ ሽያጭ ስርአት መሸጥ ነው።

28) **"የትምባሆ ምርት"** ኒኮቲን ያለባቸው እና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚውሉ በሚጨስ ወይም ጭስ በሌለው ቅርጽ የተዘጋጁ ምርቶችን ይጨምራል።

29) **"ጅምላ ሻጭ"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አከፋፋዮች፤ አስመጪዎች ወይም አምራቾች በመግዛት ለሌሎች ጅምላ ሻጮች ወይም ቸርቻሪዎች የሚሸጥ ሰው ነው፤

30) **"አዋጅ"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ነው፡፡

31) በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጐች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡ በአዋጁ ትርጉም ያልተሰጣቸው በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጐች የሚከተለውን ትርጉም ይይዛሉ፡-

produced at the Licensed Manufacturer's own factory or that of others and, includes:

a) In respect of production of beverages including spirits, beer and wine, the distilling, rectifying, compounding or denaturing of spirit.
b) In respect of tobacco, the production process from leaf products to the stage suitable for offer for consumption through smoking, snuffing, inhaling, vaping and chewing and the process to produce chewable qat, smoking tobacco, cigar, cigarettes and like products.
c) In respect of other excisable goods, extraction, changing by hand or by machine or changing of quality, nature, form, composition and assembling of a part or parts.

22) **"Market price"** means a retail price which is not calculated by a seller or buyer but determined only by the supply and demand or in the case of being unable to set a retail price, an estimated price obtained by calculation under a prescribed method.

23) **''Monthly Price List"** means monthly price list is the document submitted to MoR by each Licensed Manufacturer which provides details of the price to be used for excise purposes in the month after submission;

24) **"Place of import"** means the port, airport or land border crossing where any excisable goods enter the territory of Ethiopia.

25) **"Public holiday"** means a public holiday established by law in Ethiopia.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ:-

   ሀ) ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚያመርቱ ወይም ወደአገር በሚያስገቡ፣

   ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች በእጃቸው በሚገኝ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ወይም በማሳነስ የተከፈለባቸውን ዕቃዎች በሚያቀርቡ፣

   ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) ይህ መመሪያ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ከተዘጋጀው የአሠራር ማንዋል ጋር በአንድነት መነበብ አለበት፡፡

26) **"Retailer"** shall mean any person or business that sells excisable goods directly to the end consumer and does not typically hold such goods for resale to other retailers.

27) **"Sale"** means selling of excisable goods in cash or on credit or within a system of consignment or advance sale.

28) **"Tobacco products"** shall include all products containing nicotine that are available for human consumption, whether in combustible or smokeless form.

29) **"Wholesaler"** shall mean a person that buys excisable goods from one or more Distributors, Importers and Manufacturers, then sells them to other Wholesalers and/or Retailers.

30) **"Proclamation"** means the Excise Tax Proclamation No 1186/2020 (as amended);

31) Terms used in this Directive that are defined in the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 shall have the meaning ascribed to them in that Proclamation.

## 3. SCOPE OF APPLICATION

1. This Directive**:**

   a) is applicable to all dealers in excise goods or services, whether licensed or unlicensed.

   b) is applicable to anybody who holds excisable goods, or provides excisable services on which excise tax has not been paid, or where the excise tax has been under-declared.

2. This Directive should be read in conjunction with the Excise Tax Proclamation, an Excise Control Directive and Manufacturer's Manual which may be published by the Tax Authority to provide further details on each excise tax obligation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## ክፍል ሁለት
## ለተፈቀደላቸው አከናዋኞች ስለሚሰጥ ፈቃድ

### 4. የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት

1) ማናቸውም ሰው በገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሳይሰጠው ሲያመለክት በአዋጁ አንቀጽ 15 የተዘረዘሩትን ስራዎች ማከናወን አይችልም።
2) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጠው ፈቃድ በታክሱ ባለስልጣን እና ፈቃድ በተሰጠው ሰው እንደተደረገ ውል ይቆጠራል።
3) በፈቃዱ የተመለከተውን ግዴታ ያለመወጣት በአዋጁ አንቀጽ 39 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል።
4) ፈቃዱ የሚከተሉትን መረጃዎችየሚይዝ ይሆናል፡-
   ሀ) ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ስም፤
   ለ) ፈቃድ የተሰጠውን ሰው የመገናኛ አድራሻ፤
   ሐ) ማመልከቻ የቀረበበት ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን፤
   መ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሊያከናውን ያሰበውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ባህሪ፤
   ሠ) የየማምረት፤ የማከማቸት እና የማከፋፈል ስራ የሚከናወንባቸውን ፋብሪካዎች እና ሌሎች አግባበት ያላቸውን የስራ ቦታዎች አድራሻ፤
   ረ) የተፈቀደለት ሰው በያንዳንዱ ፋብሪከ የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች ዝርዝር፤
   ሰ) የተፈቀደለት አከናዋኝ በመሆን ስራውን የሚያከናውንበትን ስፍራ ፕላን እና ዲዛይን፤ የዚህ አይነቱ ሰነድ ጥሬእቃ፤ በከናወን ላይ ያለ ስራ እና ለፍጆታ ለመዋል የተዘጋጀ የተጠናቀቀ ምርት የሚከማችበትን ቦታ የሚያሳይ መሆን አለበት።
   ሸ) በያንዳንዱ የስራ ቦታ የተፈቀደለት አከናዋኝ የሚጠቀምባቸውን የጸደቁ መሳሪያዎች ዝርዝር፤
5) ፈቃዱ የአምራቹን አፈጻጸም መሰረት በማድረግ እንደሁኔታው ስራ ላይ የሚውሉ ሁኔታዎችን እና የውል ቃሎችን ሊይዝ ይችላል።
6) የተፈቀደለት ሰው በፈቃዱ የተዘረዘሩ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ ማዋል ያለበት በፈቃዱ ላይ የተመለከተው ፕላን በሚያሳየው ቦታ ብቻ መሆን አለበት።
7) በፕላኑ ላይ ለውጥ ማድረግ ካስፈለገ የተፈቀደለት አከናዋኝ ለውጥ ከማድረጉ በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ እና አዲሱ የስራ ክንውን ከመጀመሩ በፊት የተሻሻለ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

## SECTION II

## LICENSING OF OPERATORS

### 4. THE LICENSING REQUIREMENT

1) No person shall carry out an activity listed in Article 15 of Excise Tax Proclamation 1186/2020 without obtaining a valid licence from the Tax Authoritys.

2) The Licence is a contract between the Licensed Producer of Excise Goods and the Tax Authoritys.

3) Any failure to comply with the terms and conditions on the licence is an offence punishable under Article 39 of the Proclamation.

4) The licence will contain the following information:

   a. The name of the licensed person;
   b. The correspondence address of the licensed person;
   c. The date from which the licence is applied for to come into force;
   d. Details of the nature of excise goods and services the licensed person propose to carry out;
   e. The address of all Factories and other relevant Facilities at which the production,storage and distribution activities may be performed;
   f. A list of all equipment the licensed person is approved to use at each Factory;
   g. Plans and drawings of the premises to be used in the course of business as Licensed Operator. Such documents shall show where raw materials, work in progress and finished goods fit for consumption are stored;
   h. A list of all equipment the Licensed Operator is approved to use at each Facility.

5) The licence may contain any conditions or terms of business which may be made on a case by case basis in relation to the Manufacturer’s compliance.


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

8) ከዚህ በላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች በምእራፍ ሶስት የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟሉ እንጂ በማናቸውም ሁኔታ የሚተኩ አይደሉም።

9) ማናቸውንም ለውጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ያለማስታወቅ በፈቃዱ ከተመለከተው ውጪ የተከናወነው ስራ እንዳልተከናወነ የሚያስቆጥር እና በፈቃዱ ከተመለከተው ውጪ የሆኑ ማናቸውም እቃዎች በአዋጁ አንቀጽ 39 መሰረት የውርስ እና የቅጣት ውሳኔ እንዲወጣባቸው ሊያደርግ ይችላል።

10) የአመልካቹ የፋብሪካ የስራ ቦታ በታክሱ ባለስልጣን ሰራተኛ ሳይታይ እና አመልካቹ የተጠቀሰውን የንግድ ስራ ለማከናወን የሚያስችል የማምረቻ ቦታ እና መሳሪያ ያለው በመሆኑ ፈቃድ ሊሰጠው እንደሚገባ ማረጋገጫ ሳይቀርብ የኤክሳይዝ ፈቃድ አይሰጥም።

11) ፈቃድ ተሰጥቶአቸው በስራ ላይ ያሉ አስመጪዎች እና አምራቾች የተፈቀደለት አከናዋኝ እንደሆኑ ይቆጠራል።

12) በታክሱ ባለስልጣን የአምራችነት ወይም የአስመጪነት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ፈቃዱን ካገኙበት ቀን ጀምሮ ”የተፈቀደለት አከናዋኝ” እንደሆኑ ይቆጠራል።

13) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 11 መሰረት ፈቃድ እንደተሰጣቸው የሚቆጠር ሰዎች በሶስተኛው ሰንጠረዥ እና በአንቀስ 5 መሰረት ፈቃድ ያገኛሉ።

## 5. የተፈቀደለት አከናዋኝ የስራ ቦታ ሊያሟላቸው የሚገባ ተፈላጊ ሁኔታዎች

1) በታክሱ ባለስልጣን ፈቃድ የተሰጣቸው የተፈቀደላቸው አከናዋኞች የንግድ ስራቸውን ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከቻ ባቀረቡበት ጊዜ ባቀረቡት ፕላን መሰረት መሰረት

6) The Licensed Manufacturer may only use the equipment listed in the licence and in the areas specifically shown in the site plan.

7) If any changes are planned, the licensed Manufacturer must notify the Tax Authority prior to any change taking place and obtain a new licence showing the relevant amendments prior to any of the new operations taking place.

8) The above conditions supplement and in no way supersede the requirements of Chapter Three, Licensing of the Excise Tax Proclamation

9) Failure to notify the Tax Authority of any changes will deem the operations not covered on the existing licence as null and void and all goods, or equipment used which is not covered on a licence is liable to forfeiture and penalties under Article 39 of the Proclamation may be issued.

10) No excise licence will be issued without the applicant and factory premises being visited by an Officer who must verify the Applicant’s suitability to be licensed to undertake the relevant business and the Factory Premises and equipment is sufficient for the required operations.

11) Existing Importers and Manufacturers Deemed to be Licensed as Licensed Operators.

12) All persons licensed by the Tax Authority as Manufacturer or importer, as of date of registration shall be deemed to be “Licensed Operator” .

13) Persons deemed to have a license under sub article 11 shall obtain a revised licence as outlined at the Third Schedule and provided for at Article 5.

## 5. REQUIREMENTS FOR PREMISES OF LICENSED OPERATORS

1) Licensed Operators licensed by the Tax Authority as such must undertake business activities subject to such license at the premises for which it as



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

በተፈቀደላቸው የስራ ቦታ እና በፈቃዱ በተመለከተው ሁኔታ ማከናወን አለባቸው።

2) በተፈቀደለት አከናዋኝ ይዞታ ስር ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች በኢክሳይዝ ታክስ አዋጅ ምእራፍ አምስት መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

3) የሚቀርበው ፕላን በተፈቀደው የስራ ቦታ ጥብቅ የሆነ የደህንነት ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ መሆን አለበት። ይህም ቁጥጥር አካላዊ ቁጥጥር፤ ወደአንድ ቦታ የመግባት ቁጥጥር እና የሌብነት ወይም አስመስሎ የመስራት ጥበቃን ይጨምራል።

4) የተሟላ ጥበቃ ያለው የስራ ቦታ እንዲኖር ለማደረግ የተፈቀደላቸው የስራ ቦታዎች የደህንነት ደረጃን አክብረው መስራት አለባቸው።

5) የተፈቀደላቸው አከናዋኞች በተፈቀደው የስራ ቦታ እና በምርት አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ውስጥ ስጋት እና አደጋ የሚገመገምበትን ሆኔታ በሰነድ አስደግፈው መያዝ አለባቸው። ይህም ግምገማ ህገወጥ እቃን ወደአገር ማስገባት፤ ብከላ ወይም ያልተፈቀደ ስራ እና የመሳሰሉትን በተመለከተ ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋት፤የሚያካትት መሆን አለበት።

6) የተፈቀደለት አከናዋኝ የውጭ የደህነነት ኩባንያዎችን የሚጠቀንም ከሆነ የእነዚህ ኩባንያዎች ዝርዝር እና እና የሚያከናውኑት የደህንነት ስራ በሰነድ ተደግፎ መያዝ አለበት።

7) የተፈቀደለት አከናዋኝ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማስታወቅ እና እና ፕላኑን በተወሰነ ጊዜ ልዩነት መከለስን ጨምሮ በያንዳንዱ የስራ ቦታ የደህነነት እቅድ ሊኖረው ይገባል።

8) የተፈቀደለት አከናዋኝ ለደህንነት እና ጥበቃ ሐላፊነት ብቃት ያለው ሰው መመደብ እና የዚህን ሰው ሰም ፤ የብሄራዊ መታወቂያ ቁጥር ፤ በስራው ላይ ያለውን ሃላፊነት እና ሊሎችንም ተመሳሳይ መረጃዎች መስጠት አለበት።

9) የታክሱ ባለስላጣን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ አመልካቹ የደህነነት እቅዱን እንዲቀይር ሊጠይቀው ይችላል።

10) የታክሱ ባለስልጣን ካልፈቀደለት በስተቀር የተፈቀደለት አከናዋኝ ከጸደቀው ፕላን ውጪ ለመስራት አይችልም።

11) የስራ ቦታው በታክሱ ባለስልጣን ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ በገቢዎች ሚኒስቴር የሰደቀው ፕላን ቅጂ በስራ ቦአታው በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለበት።

provided plans and drawings in the course of the application for licence.

2) All excisable goods held by licensed Operators shall be subject to Excise Control within the meaning of Chapter Four of the Excise Tax Proclamation.

3) The plans will show what robust security measures are in place for the said premises and goods. This includes physical security, access control, and protection against theft or tampering.

4) Such licensed premises must comply with safety standards to ensure a safe working environment.

5) Licensed Operators must conduct documented risk and threat assessments for the said premises and supply chain. This should cover potential risks such as smuggling, contamination, and unauthorized access.

6) Where the licensed Operator uses external security providers, their details and the security measures they implement must be documented.

7) The licensed Operator must have a security plan in place for each site, which includes procedures for reporting incidents and reviewing the plan regularly.

8) The licensed Operator must designate a competent person responsible for safety and security and provide their full name and position in the business, as well as their personal details such as a national ID number or similar identification.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

9) The Tax Authority may at any time require the applicant to make any alteration to a plan which it considers necessary.
10) The applicant shall not deviate from an approved plan except with the written approval of the Tax Authority.
11) A copy of such plan approved by the Ministry shall be prominently displayed on the premises after the said premises have been licensed.

## 6. የአዲስ አምራቾች የንግድ ስራ መጀመር እና የማስፋፊያ ስራ

1) በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ያልተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚፈልግ ሰው የማምረት ሥራውን ለመጀመር ካቀደበት ቀን 30 ቀን በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለሥልጣን ማመልከት አለበት፡፡
2) የማመልከቻው ቅጽ አዲስ የሚጀመረውን የንግድ ሥራ በሚመለከት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሰረት የተሟላ መረጃ ማግኘት የሚያስችል መሆን አለበት፤
3) የማምረቻ ቦታው እና አመልካቹ በታክሱ ባለሥልጣን አግባብ ያለው ባለስልጣን ከመጐብኘታቸው እና አመልካቹ የማመልከቻውን ቅጽ በሚገባ ሞልቶ ከማቅረቡ በፊት ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡

## 6. COMMENCEMENT OF BUSINESS OF NEW MANUFACTURERS AND EXPANSIONS

1) Any person who is not licensed under Excise Tax Proclamation and who wishes to start a new excisable business, must apply to the Tax Authority at least 30 days prior to the expected date of commencement of the business.
2) The Application Form will require details of all aspects of the business as outlined in Article 5 of this Directive.
3) No license will be issued unless the Applicant and the Premises where the operations will be carried out have been visited by a relevant Officer and the details on the Application Form have been verified.

## 7. ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም

1) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ላይ ያልተመለከተ አዲስ ፋብሪካ ለማቋቋም ያቀደ እንደሆነ በፈቃዱ ላይ አዲሱ ፋብሪካ እንዲካተት ባማድረግ አዲስ ፈቃድ ማግኘት አለበት።
2) ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች የማምረቻ ቦታውን ጐብኝተው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት መጀመር አይችልም፡፡
3) የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ባልተሰጠው ማናቸውም የስራ ቦታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ማምረት የጀመረ

## 7. NEW FACTORIES

1) Where a Licensed Producer wishes to open a new Factory Premises which is not listed on an existing Licence, he/she must apply for the Factory to be added to the Licence and a new Licence must be obtained.
2) No person may start activities at a Factory until it has been visited by relevant MoR Officers and a Licence obtained listing the Factory details.


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ማናቸውም ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣት ይቀጣል፡፡

**8. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለበት ስነ-ስርአት**

1) ማናቸውም ፈቃድ ለማግኘት ወይም በአዋጁ አንቀጽ 16 መሰረት ለመመዝገብ የሚያመለክት ሰው የሚያቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፣

ለ) ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

(i) የታክስ ባልስልጣኑ የሚጠይቃቸውን ሰነዶች፣

(ii) የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ፣ ኮንቴይነሮች፣ መሣሪያዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣

(iii) የአሠራር ሂደቱን የሚገልፅ የፅሑፍ ማብራሪያ፣

iv) ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የእያንዳንዱን የማምረቻ ሕንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም ሕንፃው፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታ እና አካባቢውን፣

(v) የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፣

(vi) የማምረቻ መሣሪያዎችን ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፣

(vii) በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ ለማግኘት እንዲሟሉ የሚጠበቁ መሣሪያዎችን፣ የአመራረት ሥርዓት ወይም ሌላ ተፈላጊ ሁኔታ፣

3) Any person who starts production of excise goods at any premises which have not been so Licensed will be liable to administrative and criminal penalties in accordance with the Proclamation.

**8. PROCEDURES FOR LICENSING**

1. Where a person makes an application to be licensed or registered under Article 16 of the Proclamation, the application shall be:
   a) in the approved form;
   b) Accompanied by :
      i) the documents that the Tax Authority may require;
      ii) application for approval of the processes, appliances, stills, vats, vessels, utensils, pipes, and fittings for use by the applicant;
      iii) a written description of all the processes;
      iv) a plan of each building, room or place to which the application for a license relates; and the situation of each building, room or place in relation to each building, room or place in relation to other buildings, rooms or places in the vicinity;
      v) details of the installed production capacity of each production line;
      vi) evidence of installation of devices,
      vii) equipment, systems or any other similar requirements prescribed


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሐ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መሆን አለበት፡፡

2) ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በስተቀር የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አይችልም፡-

ሀ) የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሸጊያ ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት፣

ለ) ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትምባሆን ወደአገር ማስገባት፣

ሐ) ኤታኖል ወደአገር ማስገባት፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት ዕቃዎች በአስመጪነት ሊመዘገብ የሚችለው የትምባሆ ምርቶችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

4) በኤታኖል አስመጪነት ሊመዘገቡ የሚችሉት፣

ሀ) የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልበትን ምርት ለማምረት አልኮል መጠቀም የሚችሉት የኢታኖል አልኮል ወደአገር ለማስገባት መመዝገብ አለባቸው።

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው፣

ሀ) በተፈቀደው ቅጽ መሠረት፣እና

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን ከሚጠይቃቸው ሰነዶች ጋር በአንድነት መሆን አለበት፣

## 9. የማምረቻ ቦታዎችን ስለመገምገም

under the Proclamation or this directive

c) A license issued under this Directive shall be in the prescribed form.

2. A person shall not undertake the following activities unless registered by the Tax Authority-
   a) importation of cigarette paper or cigarette packaging materials;
   b) importation of raw or unprocessed tobacco; and
   c) Importation of ethanol.
3. Only persons licensed as manufacturers of tobacco products shall be registered as importers of items under sub article 1 (a) and(b) of this article
4. only persons-
   a) licenced as manufacturers of alcoholic beverages; or
   b) registered as users of spirit to manufacture unexcisable goods, shall be registered as importers of ethanol.
5. An application for registration under this Directive shall be-
   a) in the prescribed form; and
   b) accompanied by the documents that the Tax Authority may require.

## 9. INSPECTION OF PREMISES


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ የታክሱ ባለሥልጣን የማምረቻ ቦታውን እና የአመራረቱን ሂደት መገምገም አለበት፡፡

## 10. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት

1) አመልካቹ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ከቀረበ፤ ትክክለኛነታቸው ከተረጋገጠ እና የታክሱ ባለስልጣን በፋብሪካው የስራ ቦታ በሚደርገው ግብኝት ማረጋገጫ ከተገኘ በኋላ ፈቃዱ ይሰጣል።
2) ለስራ እንቅስቃሴው አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ የሚደረግን ለውጥ ማስታወቅ እንዲቻል አግባብነት ያለው የታክሱ ባለስልጣን የስራ ክፍል አድራሻ በፈቃዱ ላይ መመልከት አለበት።

## 11. የኤክሳይዝ ፈቃድን ወይም ምዝገባን ስለማገድ እና ስለመሠረዝ

1) በአዋጁ አንቀጽ 20 ከተመለከተው በተጨማሪ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው የኤክሳይዝ ፈቃድን ማገድ ይችላል፡፡

   ሀ) ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፣

   ለ) የተፈቀደለት ሰው በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆኑ ተግባራት ላይ ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣

   ሐ) ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የተከለከለ እንደሆነ፣

   መ) የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መሣሪያ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ፣

2) በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ የታገደ እንደሆነ ባለፈቃዱ፣

   ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣ እና

   ለ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚያቀርባቸው ሁኔታዎች መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

The Tax Authority shall inspect premises and processes in case of an application under Article 8 and 9 of this Directive.

## 10. ISSUE OF THE LICENCE

1) The Licence will be issued after all relevant information submitted by the Applicant has been verified and a visit has taken place by an Officer or Officers to the Factory Premises.

2) The contact details of the relevant MoR Department for the Licensed Excise Manufacturer to contact in order to notify changes in operating requirements will be clearly marked on the Licence.

## 11. SUSPENSION AND CANCELLATION OF A LICENSE OR REGISTRATION

1/ The Tax Authority may, In addition to the circumstances listed under Article 20 of the Proclamation, suspend a licence where-

   (a) a person has been found in possession of unexcised goods produced by the licensed person;

   (b) a person has been found engaging in activities not specified in the license or registration;

   (c) the licensed activity becomes prohibited by the Proclamation or any other law; or

   (d) the licensed premises or the equipment therein have been altered without the approval of the Tax Authority.

(2) Where a license or registration is suspended under the Proclamation the person shall:

   (a) Immediately cease to manufacture or import excisable goods; and



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

3) በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ወይም ምዝገባ የተሠረዘ እንደሆነ፡-

ሀ) ባለፈቃዱ፡-

(i) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ወይም ወደአገር የማስገባት ተግባሩን ማቆም፣

(ii) በእጁ በሚገኙ የኢክሳይዝ ታክስ ባልተከፈለባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል፣እና

(iii) የታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፣ ጥሬዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ቁሳቁሶች መሸጥ፣ አለበት፡፡

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን፣

(i) የተፈቀደለት ሰው በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደሌላ ቦታ እንዲያዘዋውር፣

(ii) የመንግሥትን ገቢ ለመሰብሰብ እና አዋጁን ለማስፈፀም እንዲቻል የተፈቀደለትን አምራች ፋብሪካ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ፣ ይችላል፡፡

4) ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም የታገደበት የተፈቀደለት አከናዋኝ የሚያቀረበው ይግባኝ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሰረት መቅረብ አለበት።

**ክፍል ሦስት**

**የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር**

(b) comply with any conditions that the Tax Authority may require.

(3) Where a license or registration is cancelled under the Proclamation:

(a) the person shall-

(i) immediately cease to manufacture or import excisable goods;

(ii) immediately pay all excise duty on excisable goods at hand in respect of which duty is still unpaid; and

(iii) dispose of excisable goods, materials, plant and equipment in the manufacturer’s factory in accordance with the direction of the Tax Authority;

(b) the Tax Authority may-

(i) require the licensed manufacturer to remove excisable goods in the manufacturer’s factory to another place approved by the Tax Authority;

(ii) take control of the manufacturer’s factory and of any excisable goods at the factory as may be necessary for the protection of revenue and ensure compliance with the Proclamation.

4) Any appeal against the suspension or cancellation of a Licensed Operator licence shall follow the procedures at Part Nine of the Tax Administration Proclamation No. 983/2016

**SECTION III**


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## EXCISE CONTROL

**12. የተለዩ እቃዎችን በመጋዘን ለማስቀመጥ ወይም ለሽያጭ መያዝ፡-**

1) ከዚህ በታች የትዘረዘሩትን እቃዎችን መያዝ የሚችሉት ደቃድ የተሰጣቸው አከናዋኞች ወይም አከፋፋዮች እና ጅምላ ሻጮች ብቻ ናቸው፤

ሀ) ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ አንድ በተተረጎመው መሰረት ማናቸውንም የአልኮል መጠጦች፤

ለ) ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ አንድ በተተረጎመው መሰረት ማናቸውም የትምባሆ ውጤት፤

2) የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀስ 1 በተዘረዘረው ዝርዝር ውስጥ እቃዎችን ሊጨምር ይችላል።

**12. HOLDING CERTAIN GOODS FOR STORAGE AND RESALE**

1) Only Licensed Operators and Distributors and Wholesalers may hold the following goods for further resale or distribution:

   a. All alcoholic products within the definition of such goods at the First Schedule to the Excise Proclamation, as amended.

   b. All tobacco products within the definition of such goods at the First Schedule to the Excise Proclamation, as amended.

2) The Ministry of Revenue may add further categories to the above sub article.

**13. ለማምረት ተግባር የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን እቃዎች እና ጥሬ እቃዎች በመጋዘን ሰለማኖር**

1) የተፈቀደለት አከናዋኝ ሆኖ ስራ እንዲያከናውን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፋብሪካ ያለቀለቸውን እቃዎች እና በፋብሪካው ውስጥ ለማምረት ተግባር ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥሬእቃዎችን ወይም ሌሎች እቃዎችን በታክሱ ባለስልጣን በሚወሰነው መሰረት ለኡት ማስቀመጥ አለበት።

2) የተፈቀደለት የስራ ቦታ ውዳቂ ምርቶች በታክስ ባለስልጣኑ በተወሰነው መሰረት ተለይተው መቀመጥ አለባቸው።

**13. STORAGE OF EXCISABLE GOODS AND RAW MATERIALS FOR MANUFACTURE THEREOF.**

1) The finished product of a factory licensed as a Licensed Operator shall be stored separately from the raw materials or other goods to be used in manufacture in the said factory as specified in the plan approved by the Tax Authority.

2) The waste products of a licensed premises shall be stored separately as specified in the plan approved by the Tax Authority.

**14. ውዳቂ ምርቶችን በመጋዘን መያዝ እና ማስወገድ**

1) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በምርት ሂደት ውስጥ የባከኑ ወይም በመጋዘን ውስጥ የተበላሹ እቃዎችን መልሶ ለመሸጥ በተፈቀደለት የሳራ ቦታ መያዝ ይችላል። የዚህ አይነት ውዳቂ ምርቶች በትርፍነት የተቆረጡ፤ ጊዜ ያለፈባቸው እና የተበከሉ ወይምበማናቸውም መንገድ ለሰው ልጅ ፍጆታ ሊውል በማይችል አኳኋን የተበላሹትን ይጨምራሉ።

**14. STORAGE AND DISPOSAL OF WASTE PRODUCTS.**

1) The licensee shall keep on the licensed premises such waste products from production processes or arising from the storage for resale. Such waste products shall include but are not limited to byproducts, excess cuttings, expired



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

2) እነዚህ ውዳቂ ምርቶች በተለየ ሁኔታ በሚጠበቅ ቦታ መቀመጥ አጋባበንት ባለው ማስታወቂያ በተመለከተው መሰረት መረጃ ሊያዝላቸው ይገባል።
3) ማናቸውም በተፈቀደለት የስራ ቦታ የሚከኝ ውዳቂ ምርት በኤክሳይዝ ታክስ ከፍተኛ ሃላፊ ሳይፈቀድ ሊቃጠል ወይም በሌላ መንገድ ሊወገድ አይችልም።
4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ መሰረት እንዲወገድ ውሳኔ የተላለፈበት ውዳቂ እቃ የኤክሳይዝ ታክስ ከፍተኛ ሀላፊ በጽሑፍ በሰጠው መመሪያ በተመለከተው መሰረት መወገድ አለበት።

## 15. የኤክሳይዝ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ያስራ ቦታዎች

1) ከኤክሳይዝ ታክስ ሃላፊ ካልተፈቀደ በስተቀር በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በተፈቀደለት መጋዘን ውስጥ ሊቀመጥ አይችልም።
2) የታክሱ ባለስልጣን ወደአከፋፋዮች፤ ጅምላ ሻጮች እና ቸርቻሪዎች መጋዘን ውስጥ የሚገባ ማናቸውም ማሸጊያ እና መጠቅለያ ባለስልጣኑ በሚያዘው መሰረት የመለያ ምልክት እንደረግባቸው ሊያዝ ይችላል።
3) በእቃው ላይ ለሚደረገው ቁጥጥር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ወደተጠቀሰው የስራ ቦታ የሚገባ ማሸጊያ እና መጠቅለያ በኤክሳይዝ ታክስ ሀላፊ በተወነው መሰረት መቀመጥ ወይም መደርደር አለበት።
4) የኤክሳይዝ ታክስ ሀላፊ የተፈቀደለት አከናዋኝ የታክስ ባለስልጣኑ በሚወስነው መሰረት በእያንዳንዱ የተፈቀደለት የስራ ቦታ የሚገነው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች መደርደሪያ፣ ጥቅል፤ስብስብ፤መጠቅለያ ስቶክ ካርድ ውይም ሌላ መለያ እንዲዘጋጅለት ሊጠይቅ ይችላል።
5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት የሚያዘው ስቶክ ካርድ የመድረደሪያውን፤ የጥቅሉን፤ የስብስቡን የመጠቅለያውን እና የሌላውን መያዣ የተሟላ ስም እና ትክክለኛውን የሂሳብ ቁጥር የያዘ መሆን አለበት።
6) የተፈቀደለት አከናዋኝ በካርዱ ወይም በመለያው ላይ ያለው ቁጥር መለወጡን እንዳወቀ ወዲያውኑ የሂሳብ ቁጥሩን መለወጥ አለበት።

products and contaminated or otherwise compromised products that are deemed unfit for human consumption.

2) Such waste products shall be stored in a separate secured area, and records maintained in the form required in the relevant Notification.
3) No waste products of a licensed premises may be destroyed or otherwise disposed of except with the written permission of a senior officer of excise.
4) The waste products permitted to be destroyed under sub-paragraph (3) shall be destroyed in such manner as the senior officer of excise may in writing, direct.

## 15. PREMISES TO BE SUBJECT TO CONTROL PROCEDURES

1) No goods other than the goods specified in the licence shall be stored in any licensed warehouse, unless the prior permission of the senior officer of excise in that behalf has been obtained.
2) The Tax Authority may require that packages or containers entering the premises of Ditributers, Wholesellers and Retailers shall be marked with such identification marks and in such manner as the Notification specify.
3) Packages or containers entering the premises mentioned under sub-article 2 of this Article shall be placed or stacked in such manner as a senior officer of excise may direct, for the purpose of facilitating the inspection and checking thereof.
4) A senior officer of excise may require a Licensed Operator to affix to every lot, stack, bale, bundle, package or other container of exciseable goods held by the said licensee on the licensed premises a stock-card or other label, in physical or electronic form as the Tax Authority may by Notification specify.
5) Such stock-card or label shall give a full name and true account of the contents of the lot,


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

**16. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ**

1) የተፈቀደለት ሰው፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌላም አስፈላጊ ቦታ ላይ በአማርኛና በአካባቢው የሥራ ቋንቋ፡-

(i) "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ" እና

(ii) የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት፡፡

ለ) በምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሐ) የማከማቻ እና የማስተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠየቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

መ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጁባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሣሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

ሠ) የተፈቀለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

stack, bale, bundle or other container to which it is affixed

6) The Licenser Operator shall alter the account contained in such card or label as soon as it becomes aware of any change in the contents of the said lot, stack, bale, bundle or other package.

**16. MARKING OF PREMISES AND PIPES**

1) A licensee shall-

(a) at the principal entrance and such other prominent place as the Tax Authority may require mark in Amharic and other official language-

i) the words "EXCISE PREMISES"; and

ii) the name of the licensed person and the license number allocated to the premises.

(b) ensure that the pipes in the production process are joined permanently and easily examined along the whole length;

(c) ensure that the pipes and vessels conform to the standards specified for that industry;

(d) mark and maintain in oil colors each item of plant used in the manufacture, preparation for sale, or storage of materials or excisable goods;

(e) to the satisfaction of the Tax Authority, place and keep each vessel and utensil in a convenient situation easy to access for official examination and account, and so fixed as to admit of the content thereof being accurately gauged or metered;

(f) provide all such fittings as may be required by the Tax Authority for the attachments of



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ረ) ለኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ ሲባል መቆለፍ ወይም ማሸግ እንዲቻል የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት መሣሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ሰ) የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ፡-

(i) በእያንዳንዱ የማምረት ሂደት የምርት ርክክብ የሚፈፀምባቸው የማስተላለፊያ መስመሮች በተለያየ የዘይት ቀለም እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይጠፋ በየጊዜው እንዲታደስ ማድረግ አለበት፡፡

(ii) ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም፣ አለበት፡፡

ሸ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሰ) አፈፃፀም የማጣሪያ ፋብሪካ ባለቤት በተሟላ አኳኋን እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፊያ መስመሮችን የሚከተለውን የዘይት ቀለም ዓይነት መቀባት አለበት፡-

(i) የአልኮል መጠጥ - ቀይ

(ii) ቢራ - ሰማያዊ

(iii) ሞላሰስ - አረንጓዴ

(iv) የሚጠራ ወይን - ቡናማ

(v) ውሃ - ቢጫ

(vi) ናፍጣ - ጥቁር

ቀ) ለታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስታወቅ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የአመራረቱን ሂደት ወይም አካሄዱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሣሪያ መጨመር፣ የለበትም፡፡

2) ሀ) በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ የጽሕፈት ሥራ የሚከናወንበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬዕቃ መጋዘን፣ የምርት መጋዘን የተለያየ መሆን አለባቸው፡፡

revenue locks or seals to secure the factory and plant for excise purposes;

(g) to the satisfaction of the Tax Authority—

i) paint and maintain so painted, in different oil colours, pipes used for delivery of products at each stage of manufacturing; and

ii) place and keep each vessel and utensil in a convenient situation easy to access for official examination and account, and so fixed as to admit of the content thereof being accurately gauged or metered.

(h) for purposes of (1) (g) of this Article, a distiller shall paint on the full length or in bands of suitable intervals on pipes for conveyance of-

i) Spirit -Red

ii) Wash/worts- Blue

iii) Molasses- Green

iv) Low wines of feints- Brown

v) Water- Yellow

vi) Fuel oil- Black

(i) not vary any process or alter move, or add to the vessels, utensils pipes or fittings in the factory unless the person has given prior notice in writing to the Tax Authority and has obtained the Tax Authority's approval of all such variations alterations, movements or additions.

2)

(a) A Licensed premises shall provide for separate



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ለ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) አፈፃፀም ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበው ቦታ ጥበቃ የሚደረግለት እና አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስን በሚገባ መሰብሰብ እንዲቻል ለይቶ ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ የሚያስችል አካል የተገጠመለት መሆን አለበት፡፡

3) ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የተፈቀደለት ሰው እና የተመዘገበ አስመጪ ወደ አገር የሚያስገባቸውን ዕቃዎች የሚያከማችበት በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደ የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፡፡

office accommodation, production area, raw materials storage and finished goods storage.

(b) For purposes of (2) (a) of this Article , the areas shall be secure and isolated from each other, and fitted with attachments for revenue locks or seals to secure for excise purposes.

3) Where a person is licensed as a manufacture of excisable goods and is also registered as an importer of excisable goods, that person shall provide separate premises or storage rooms approved by the Tax Authority for storage of the imported goods.

## 17. የተፈቀደለትን አከናዋኝ የስራ ቦታ መከታተል

1) የታክሱ ባልስልጣን ለመንግስት ገቢ ትክክለኛ አሰባሰብ ሲባል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አግባብነት ያለው ሰራተኛ የተፈቀደለትን አከናዋኝ የስራ ቦታ በሙሉ ወይም የተወሰነውን የስራ ቦታውን ክፍል እንዲቆልፍ፤ እንዲያሽግ ወይም ሌላ ማናቸውንም የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ እና/ወይም የፈሳሽ መለኪያን ፤ ካሜራን፤ አውቶማቲክ ባር ኮድ ፤ስካነር እና በኮምፒውተር የታገዘ ስካን እና የመሳሰሉትን እንዲጠቀም ሊያደርግ ይችላል።

2) የዚህ አይነቶቹ ቁልፎች፤ማሸጊያዎች፤ የመከታተያ መሳሪያዎች ፤ የቁጥጥር ስርአቶች ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎች ወጪ የሚሸፈነው በተፈቀደለት አከናዋኝ ሲሆን ዝርዝሩ በማስታወቂያ ይገለጻል።

3) ቁልፍ እና ማሸጊያ የተድረገው በውጪው መዝጊያ ወይም መዝጊያዎች ላይ ወይም በስራ ቦታው ክፊል ላይ ከሆነ፤ አግባበነት ያለው የኤክሳይዝ ሰራተኛ በማናቸውም ጊዜ የቀልፉን እና የመሽጊያውን ደህነነት ለማረጋገጥ ወደተቆለፈው ወይም ወደታሸገው ወይም ሌላ የጥንቃቄ እርምጃ ወደተወሰደበት ቦታ ሊገባ ይችላል።

4) አግባበነት ያለው የተፈቀደለት አከናዋኝ በታክስ ባለስልጣኑ ተፈላጊ የሆነውን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በስራ ቦታው ላይ የሚደረገውን ክትትል ለማከናወን ለሚያስፈልገው የቁጥጥር ስርአት እና ቴክኖሎጂ አጋዥ የሆነውን አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈለውን የኔትወርክ ክፍያ ወይም የኢንተርኔት ወጪ ይሸፍናል።

## 17. MONITORING OF PREMISES OF LICENSED OPERATORS

1) The Tax Authority may direct the proper officer to place such locks, seals or other safeguards, and/or implement such monitoring devices and control processes, including but not limited to flow meters, cameras, automated barcode scanners, computerised scanning equipment, etc., as may be deemed necessary for the protection of the revenues of the State upon any part of the premises of licensed Operators or upon any portion of the plant contained therein.

2) Such locks, seals, monitoring devices, control processes or safeguards shall be provided at the expense of the Licensed Operator and will be laid out in an appropriate Notification.

3) Where locks, seals or other safeguards are placed upon the outer door or doors or any portion of the plant of a licensed premises, the proper officer shall have access at all times to such door or doors or any portion of the plant



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

5) የታክሱ ባለስልጣን የተፈቀደለትን አከናዋኝ የስራ ቦታ ለመከታተል በራሱ ውሳኔ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ከሩቅ የመከታተያ ቦታዎችን ሊያቋቋም ይችላል።

6) የምርት ብዛትን ወይም ሌሎች መሳሪያዎችን ለመለካት በተፈቀደለት የስራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሜትሮች ወይም መሳሪያዎች በታክሱ ባለስልጣን የተፈቀዱ እና የዚህን መመሪያ አንቀጽ 23 ድንጋጌ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም በታክሱ ባለስልጣን አቅራቢነት ፈቃድ የተሰጣቸው ዝርዝር በየጊዜው ይፋ መደረግ አለበት። ፈቃድ የተሰጣቸው አቅራቢዎች፡-

ሀ) የተፈቀዱ ሜትሮችን ወይም መለኪያዎችን በሚገባ መያዝ አለባቸው። የእነዚህን እቃዎች አያያዝ የሚያሳይ መረጃ በተፈቀደለት የስራ ቦታ ማስቀመጥ እና አግባብ ያለው የታክስ ባለስልጣኑ ሰራተኛ ሲጠይቅ ለምረመራ ማቅረብ አለባቸው፡

ለ) ሜትሮች እና መለኪያዎች በትክክል የሚሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ በየጊዜው ፍተሻ ሊደረግባቸው ይገባል፤

ሐ) ለወደፊት በሚገለጸው የአሰራር ስርአት መሰረት ከታክስ ባለስልጣኑ የመከታተያ ማእከል ጋር ያለው የግንኙነት መስመር ያልተቋረጠ ስለመሆኑ በየጊዜው መፈተሽ አለባቸው።

7) በሜትሮች ወይም መለኪያዎች ላይ የሚደርስን ጉዳት ወይም የስራ መታወክ የተፈቀደለት አቅራቢ ወዲያውኑ ለታክሱ ባላስልጣን ሰራተኛ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል። የዚህ አይነቱ ሜትር ወይም መለኪያ ከመጠገኑ ወይም በሌላ ከመተካቱ በፊት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

**18. ፋብሪካውን በሩቅ መቆጣጠር የሚያስችል መሣሪያ ስለመግጠም**

for the inspection of the locks, seals or other safeguards thereon.

4) The relevant Licensed Operator will be responsible for any fees for network or internet access necessary to enable the continuous monitoring of licensed premises in accordance with the control processes and technology required by the Tax Authority.

5) The Tax Authority may implement at its own discretion one or more remote centres to monitor the premises of Licensed Operators.

6) All meters or devices used for measuring the production of goods, or other equipment used for monitoring purposes at licensed premises must be approved by the Tax Authority, and must comply with the requirements of Articles 21 and 23 of this Directive. Vendors of such equipment shall apply to the Ministry for approval, and an approved vendors list shall be notified from time to time.Approved vendors shall:

   a. ensure that all meters or devices approved are properly maintained. A record of such maintenance shall be kept on the licensed premises and shall on demand be produced for inspection of a proper officer.
   b. cause all meters and devices to be regularly tested for accuracy.
   c. periodically test connectivity with the Tax Authority monitoring centre(s) in accordance with testing protocols to be notified in due course.

7) Any damage to or malfunction of any meter or device shall be reported immediately by the approved vendor to the proper officer. Such meter or device shall not be used until it is repaired or replaced

**18. REQUIREMENT TO PROVIDE REMOTE VIEW OF THE FACTORY**



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

1) የተፈቀደለት ሰው በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት መግጠም አለበት፡፡
2) የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት ሊገጠም የሚገባውን የቴክኖሎጂ መሣሪያ ዝርዝር ባህሪያት ይወስናል፡፡
3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ፋብሪካውን በሩቅ ማየት የሚያስችለውን የቴክኖሎጂ ሥርዓት የመጠቀም ያልተገደበ መብት ይኖረዋል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የቴክኖሎጂ ሥርዓት የታክስ ባለሥልጣኑ በሚጠይቀው መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀ የምስል ማከማቻ እና ምስልን እና ሌላን መረጃ በዲጂታል ሥርዓት በቀጥታ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

## 19. የአመራረት ሂደትን በቴክኖሎጂ ስለማስደገፍ

1) የታክሱ ባለሥልጣን የተወሰኑ የተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች በእያንዳንዱ ደረጃ ያሏቸው የአመራረት ሂደት በአውቶማቲክ የአመራረት ሂደት የታገዘ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2) የአልኮል መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎችን በሚመለከት ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ግዴታ ሊጣልባቸው የሚችለው የፋብሪካው የማምረት አቅም በሰዓት ከ500 (አምስት መቶ) ጠርሙስ በላይ ሲሆን ነው፡፡

## 20. የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች

1) የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት በማምረቻ ቦታዎች ሊታከሉ የሚገባ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት በጋዜጣ እና በድረገፁ ላይ ማሠራጨት አለበት፡፡
2) በታክሱ ባለሥልጣን የሚፈቀዱት በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ የግብዓቶችን እና የአላቂ ዕቃዎችን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3) የጥሬዕቃ እና የአላቂ ምርቶች ማከማቻ ጋኖች በጋኑ ውስጥ ያለውን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡
4) በዚህ መመሪያ መሠረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው

1) A licensee shall install systems to enable a remote view of the operations of the factory.
2) The Tax Authority shall prescribe the specifications of the systems required under this Directive.
3) For purposes of sub article (1) of this article, the Tax Authority shall have unlimited access to the system.
4) The systems referred to in sub-article (1) of this Article, shall be capable of storing and transmitting real-time digital images and such other information through a secure platform as the Tax Authority may require.

## 19. AUTOMATION OF PRODUCTION

1) The Tax Authority may require a licensed premise to have an automated production process at every stage of manufacturing for specific industries.
2) For purposes of this Article manufactures of alcoholic beverages, the installed production capacity shall not be less than 6,000 bottles per hour.

## 20. METERING AND MEASURING DEVICES

1) The Tax Authority shall by notice in a newspaper and its website specify the requirements of a measuring or metering device and such other equipment as may be required under this Diretive.
2) The production system measuring and metering devices approved by the Tax Authority to allow full accounting of raw materials, intermediate goods and the finished products.


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

መሠረት በምርቱ ሂደት በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው፡፡

5) የተፈቀደለት ሰው፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን ለሚያካሂደው ቁጥጥር እና ስሌት በሚያመች መንገድ መቁጠሪያ እና መለኪያ ያላቸውን ጋኖች ወይም ማከማቻዎች የማዘጋጀት፣ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፣ እና

ለ) በመለኪያ እና በመቁጠሪያ መሣሪያዎች ላይ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የተደረገውን ዕድሳት የሚያሳይ መዝገብ የማዘጋጀት፣ መሣሪያዎቹ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## 21. ኢንስፔክሽን

1) አግባበነት ያለው የታክስ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ሹም ወይም ለዚህ ስራ በከፍተኛው የኤክሳያዝ ሹም ውክልና የተሰጠው ሌላ ማናቸውም ሰራተኛ በማናቸውም ጊዜ የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች እና የእነዚህን ጥሬእቃዎች ወይም በተፈቀደለት ስራ አከናዋኝ የስራ ቦታ የተገኘን ሌላ ማናቸውም እቃ ለመመርመር፤ ኢንስፔክት ለማድረግ፤ለመመዘን እና ለመለካት እንዲሁም በተፈቀደለት አከናዋኝ፤ በአከፋፋይ፤ በጅምላ ሻጭ ወይም ቸርቻሪ የስራ ቦታ የተገኙ ማናቸውንም ማሸጊያዎች እና መያዣዎች እና በውስጣቸው ያለውን እቃ ለመመርመር ይችላል።

2) በኤክሳይዝ ታክስ ከፍተኛ ሹም በተጠየቀ ጊዜ የተፈቀደለት አከናዋኝ፤ አከፋፋይ፤ ጅምላ ሻጭ ወይም ቸርቻሪ፡-

ሀ) በዚህ መሪያ አንቀጽ 15 እና 16 የተዘረዘሩ የሂሳብ መዝገቦችን፤መረጃዎችን እና መዝገቦችን እና ግብይት የተፈጸመባቸውን የክፍያ መጠየቂያዎች፤ደረሰኞች ወይም ሌሎች ሰነዶች እና ለተፈቀደለት ስራ አከናዋኝ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት እንዲይዝ የሚጠበቁ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት።

ለ) ለማምረት ተግባር እንዲውሉ በስራ ቦታው የተከማቹ የተያዙ ወይም በርሱ ቁጥጥር ስራ ያሉ ጥሬእቃዎችን

3) The raw materials and finished products storage tanks shall be fitted with tank gauging systems to allow proper account of the contents therein.

4) The metering and measurement devices required under this Directive shall be installed in such places in the production line as the Tax Authority may specify for each production facility.

5) A licensee shall-

a. provide and regularly maintain accurately calibrated, metered and gauged tanks and vessels to enable easy examination and account of the content therein by the Tax Authority; and
b. Keep maintenance logs for metering and measuring devices and ensure that they are accurately calibrated at least once every year.

## 21. INSPECTION

1) Any senior officer of excise at the relevant Tax Authority branch office or any officer of excise deputed for that purpose by the said senior officer of excise may at any time examine, inspect, weigh, and measure the stock of exciseable goods or raw materials or any other goods held in the premises of licensed Operators and may inspect every package or container found on any of the Licensed Operator, Distributor, Wholeseller or Retailer and the contents thereof.

2) If so demanded by a senior officer of excise a Licensed Operator, Distributor Wholeseller or Retailer shall-

a. produce for inspection such of the books, records and registers as are prescribed at paragraphs 15 and 16 and all bills, invoices or other documents



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

እና እቃዎችን ብዛት እና መገለጫ የሚያሳይ በጽሁፍ የተዘጋጀ ሰነድ፤

relating to any transaction entered, and any documents or records required to be kept in pursuance of any condition endorsed on the relevant Licensed Operator;

b. render an account in writing of the quantity and description of raw materials and other goods to be used in manufacture in his possession, custody or control and the places or premises in which the said raw materials and goods are kept.

**22. በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት ስለማድረግ**

1) ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማሸጊያዎች ለመከታተል እና ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡
2) ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚይዝ እያንዳንዱ ማሸጊያ ወይም መያዣ ወይም መጠቅለያ በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል፡-

   ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን አገር የሚያሳይ ፅሑፍ፣

   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣ "ለአገር ውስጥ ፍጆታ" የሚውል የሚል ፅሑፍ፣

   ሐ) ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ "ከታክስ ነፃ" የሚል ፅሑፍ፣

3) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ዕቃዎችን ለመለየት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

**22. MARKING OF PRODUCTS, CONTAINERS AND PACKAGES**

1) All packages of excisable goods including those meant for duty free, exports and other excisable goods shall bear distinct markings to enable the goods to be trackable and traceable.
2) Each package or container and material wrapping the package for wholesale purposes shall have printed on it—
   a) in the case of exports, the country of final destination;
   b) in the case of excisable goods for consumption in Ethiopia,"FOR USE IN ETHIOPIA";
   c) in the case of excisable goods for sale to duty free shops, or Diplomatic shops, "DUTY FREE";
3) For purposes of this Directive, the Tax Authority may specify other markings to distinguish excisable goods meant for different persons.

**23. በጥሬዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር**

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውሉ ጥሬዕቃዎች መጠናቸውን በትክክል ለማወቅ

**23. CONTROL OF RAW MATERIALS**



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ለሚደረገው ቁጥጥር በሚያመች አኳኋን ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን መቀመጥ አለባቸው፡፡

2) በተፈቀደለት ማምረቻ ውስጥ ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይችልም፡፡

3) የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቲል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው መሠረት ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይችልም፡፡

1) Raw materials used for manufacture of excisable goods shall be entered into a secure room or storage facility and stored in a manner to allow taking of full account of the materials therein.

2) A person shall not remove any raw materials for a purpose other than manufacture in the licensed premises without the approval of the Tax Authority.

3) A distiller shall not store any alcohol, other than potable ethyl alcohol, unless it is denatured in accordance with the Directive to be issued by the Tax Authority.

## 24. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ" በመባል ወደሚታወቅ ክፍል መዘዋወር እና በዚህ መመሪያ መሠረት ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውጪ እስከሚደረጉ ድረስ በዚሁ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ሆኖም የተጣራ አልኮል መቀበያ ጋኖች የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ እንደሆኑ ይቆጣራል፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል በር ላይ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል" የሚል ፅሑፍ መለጠፍ አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የተመረቱ ዕቃዎች ከማከማቻነት ውጪ ለሌላ ለማናቸውም ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም፡፡

4) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለቆጠራ በሚያመች አኳኋን በኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

5) ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት ዕቃ መያዣ ጠርሙስ ወይም ማሸጊያ አምራቹን ለይቶ ማወቅ የሚያስችለው ልዩ ምልክቱ (ሌብል)፣ የአምራቹ ስም፣ የተመረተበት ቦታ እና ቀን፣ አድራሻው፣ የተከታታይ ምርት ቁጥር፣ የባር ኮድ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምልክት ሳይደረግበት በፊት ከኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ማውጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

6) ለውጭ ገበያ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ሊሸጡ የተመረቱ ዕቃዎች ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች መንገድ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

## 24. STORAGE AND DELIVERY OF EXCISABLE GOODS AFTER MANUFACTURE

1) All excisable goods shall, after the process of manufacture has been completed, be forthwith removed to a room which shall be known as the "excise stock room"; and the goods shall be kept therein until delivery therefrom is made in accordance with this Directive. Provided that for distilled spirit, the receiving tanks shall be deemed to be the excise stock room.

2) The excise stock room shall be clearly marked with the words "EXCISE STOCK ROOM".

3) The excise stock room shall not be used for any purpose other than of storing finished excisable goods after they have been manufactured.

4) The excisable goods in a stock room shall be stored in such a manner to facilitate the taking of a full account of the them.

5) No person shall remove, or cause, or allow to be removed, to or from the excise stock room any excisable good unless the bottle or container has


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

7) የተፈቀደለት ሰው ከተሸጡ በኋላ ወደተመረቱበት ፋብሪካ የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፡፡

## 25. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ከታክስ ነፃ ሆነው የሚሸጡ ዕቃዎች

1) የተፈቀደለት ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካጋጠሙ በዕቃዎቹ ላይ ታክሱን እንዲከፍል ይገደዳል፡-

ሀ) ለውጭ ገበያ የተመረቱ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተሸጡ እንደሆነ፣

ለ) ከታክስ ነፃ ሆነው ስለሚሸጡበት ወይም ታክሱ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በአዋጁ የተመለከተው ያልተሟላ እንደሆነ፣

2) የተፈቀደለት ሰው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና የተከፈለባቸው ታክስ ተመላሽ የሚደረግ ዕቃዎችን የማስታወቅ እና የማጓጓዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

3) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ የአልኮል መጠጦችን የሚሸጥ የቀረጥ ነፃ መደብር እነዚህን ዕቃዎች ወደአገር ለማስገባት የሚችለው "ከቀረጥ ነፃ" የሚል ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## 26. የሂሳብ መዝገብን ስለመያዝ

1) የተፈቀደለት ሰው በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2016 ድንጋጌዎች መሠረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንተጠበቀ ሆኖ፤ የተፈቀደለት ሰው በተፈቀደለት የስራ ቦታ የሚከተሉትን በሚመለከት ስም እና ትክክለኛውን ሂሳብ የያዘ የሂሳብ መዝገብ ወይም ሰነድ መያዝ አለበት፡-

printed on its main label the name of the brand, the manufacturer, the place and date of manufacture, address, batch number, bar code or any other markings that relates the product to the licensee.

6) Goods manufactured for export or exempt from excise duty shall be stored separately from other goods in the excise stock room in a manner to allow easier examination and taking account of the goods.

7) A licensed person shall provide a separate storage for excisable goods returned to the factory in which they were manufactured.

## 25. EXCISABLE GOODS FOR EXPORT AND EXEMPTION

1) A licensee shall be liable for the payment of excise duty in respect of excisable goods-

   a) manufactured for export which are diverted into or offered for sale in Ethiopia; and

   b) used inconsistent with conditions of exemption, remission or refund under the Proclamation.

2) licensed person shall be responsible for declaration and transportation of excisable goods destined for export or under remission, exemption or refund.

3) A duty-free store that sells alcoholic beverages exempt from excise tax may only import these items if they are marked "duty-Free".

## 26. MAINTENANCE OF RECORDS

1) A licensee shall keep records as required under the Proclamation and the Tax Administration Proclamation No 973/2016 .

2) Notwithstanding the generality of sub-article 1 of this Article the licensee shall at all times keep on



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

i) በተፈቀደለት የስራ ቦታ ለማምረት ተግባር እንዲውሉ በመጋዘን የተቀመጡ ለምርት የሚውሉ ጥሬእቃዎችን እና ሌሎች እቃዎችን፤

ii) በማምረት ሂደት ላይ ያሉ በከፊል የተጠናቀቁ እቃዎችን፤

iii) ውዳቂ ምርቶችን፤

iv) አግባበነት ካለው የኤክሳይዝ ምልክትን ጨምሮ ከስራ ቦታው የወጡ ያለቁ ምርቶችን፤በመጋዘን ያሉ እና የተወገዱ ምርቶችን

3) የዚህ አይነት መረጃዎች የስራ ቦታው ስራ ከማቆሙ በፊት ካለው የሙሉ ቀን ወይም የግማሽ ቀን በፊት በሂሳብ መዝገብ ወይም በሰንድ ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፤የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው የተረከባቸውን ወይም ከስራ ቦታው ወጪ ያደረጋቸውን እቃዎች ብዛት እና መግለጫ መያዝ አለባቸው፡፡

4) የተፈቀደለት ሰው አግባበነት ያለው የታክሱ ባላስልጣን ቅርንጫፍ የኤክሳይዝ ታክስ ሰራተኛ የሚጠይቀውን የመጋዘን መግለጫ እና የመሳሰሉትን መስጠት አለበት።

5) መጋዘን እና የማከፋፍያ ቦታ ያለው የተፈቀደለት ስራ አከናዋኝ አግባብ ላለው የታክሱ ባላስልጣን ቅርንጫፍ የኤክሳይዝ ሰራተኛ ከየወሩ መጨረሽ አስረኛው ቀን ሳይዘገይ የኤክሳይዝ ታክስ ሰራተኛ በሚጠይቀው መሰረት በተጠናቀቀው ወር ውስጥ ወደተፈቀደለት የስራ ቦታ የገባውን እና ከስራ ቦታው የወጣውን እቃ የሚያሳይ መረጃ ይሰጣል።

6) በዚህ መመሪያ የተደነገው ቢኖርም የታክሱ ባለስልጣን በማናቸውም ጊዜ የተፈቀደለት ሰው ለጥሬእቃ፤ ለለባከነ ምርት፤ ለማምረት ተግባር ለሚውሉ እቃዎች እና ለተጠናቀቀ ምርቶች ሊደርግ ሰለሚወስደው የጥንቃቄ እርምጃ በጽሁፍ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መያዝ ያለበት የሂሳብ መዝገብ፣

ሀ) በሚነበብ እና ሊጠፋ በማይችል አኳኋን በጽሕፈት መሣሪያ የተዘጋጀ፣ የታተመ ወይም የተፃፈ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ ከመፅደቁ በፊት የተደረገ እርማት ወይም ለውጥ ሲኖር የተደረገውን ለውጥ ወይም እርማት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል፣ እርማቱን ያከናወነው ሰው ፊርማ እና የታረመበት ቀን የተፃፈበት፣

ለ) በተፈቀደ አኳኋን በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መንገድ የተዘጋጀ እና በተፈቀደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ለውጥ ያልተደረገበት፣

መሆን አለበት፡፡

8) የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጪ የተዘጋጀን የሂሳብ ሰነድ ወይም ማስረጃ

the licensed premises books and records wherein are entered a full and true account of the particulars relating to-

i) raw materials and other goods to be used in manufacture received into the licensed premises, issued for manufacture, and kept in stock;
ii) semi-finished or partly finished products in the course of manufacture;
iii) waste products; and
iv) finished products manufactured, stored and removed, with full records of the relevant Excise markings from the licensed premises.

3) Such books and records shall be entered daily before the premises are closed for operations at the end of the full day or any half day of work and shall contain particulars as to the quantity and description of dutiable goods which have been received into or removed from the premises.
4) The licensee shall submit to a senior officer of excise of the Tax Authority branch such stock statements as the said officer may require.
5) Licensed Operator that operate Warehouse and Distribution premises shall deliver to the senior officer of excise of the Tax Authority branch not later than the tenth day of each month a return, in such form as the said officer may require, of all receipts into and removals from the licensed premises during the last preceding calendar month.
6) Notwithstanding any other provisions in this Directive the Tax Authority may at any time in writing order safeguards to be taken by the licensee for the keeping and securing the safety of the raw materials, waste products, goods to be used in manufacture, and the finished product in the licensed premises.
7) The records required in sub article (1) of this Article


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ላለመቀበል ወይም በዚህ ሰነድ መሠረት ሥራዎችን ላለማከናወን ይችላል፡፡

9) የታክሱ ባለሥልጣን ማናቸውም የሂሳብ ሪፖርት ሊቀርብ የሚገባበትን ቅጽ ወይም ለአዋጁ እና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተቀባይነት የሚኖራቸውን ሰነዶች ዓይነት ሊወሰን ይችላል፡፡

shall be:

a) printed, typed or written thereon indelibly and legibly, and every alteration in the form or document made prior to its acceptance shall be made in such manner as to leave the error as well as the alteration legible; and every such alteration shall be initialled and dated by the person making it; or
b) in electronic form or other form which shall be made in such a manner as may be approved, and shall not be altered except in the prescribed manner.

8) The Tax Authority may decline to accept or to act upon any form, document or records submitted to him unless the requirements of the Proclamation and this Directive in relation thereto have been observed
9) The Tax Authority may specify the form of any other document required or authorized for the purposes of the Proclamation and this Directive.

## 27. የምርት መለያን ስለማሳወቅ

1) ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው እና በሚያፀድቀው ዝርዝር መሠረት ልዩ ምልክቱን ሳያስታውቅ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ለሽያጭ በጠርሙስ ወይም በሌላ መያዣ ማሸግ አይችልም፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት ሁኔታዎችን በመወሰን የተፈቀደለት ሰው ለሙከራ የሚውሉ ምርቶችን እንዲያመርት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 27. DECLARATION OF BRANDS

1) No licensee shall bottle or otherwise pack any excisable goods for sale unless a declaration has been made to the Tax Authority in the prescribed format and containing such particulars as the Tax Authority may require and the Tax Authority has approved.
2) Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this Article, the Tax Authority may upon application, authorize a person to carry out experimental operations subject to such conditions



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

as the Tax Authority may impose.

## 28. የምርት መከታተያ ሥርዓት

1) የታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የምርት ሂደቱን መከታተል የሚያስችል የሂሳብ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያዝ ይችላል፡፡
2) የምርት መከታተያው ሥርዓት፡-
   ሀ) የምርትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ወይም ማሳየት የሚያስችል መሣሪያ፣
   ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን በተፈቀደለት አምራች የተመረቱ ወይም ወደአገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ብዛት ለመቆጣጠር፣ ለመመዝገብ እና መረጃውን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሣሪያ፣ መሆን አለበት፡፡
3) የምርት መከታተያው ሥርዓት፡-
   ሀ) በማምረቻው ቦታ በምርት ሠንሰለት ውስጥ በእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የማተሚያ መሣሪያ ላይ ሊገጠም፣ እና
   ለ) ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር በታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን ሊገጠም፣ ይገባል፡፡
4) አዲስ ወይም የተሻሻለ የምርት መከታተያ ሥርዓት መግጠም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው መሣሪያው ከሚገጠምበት ጊዜ በፊት የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡-
   ሀ) አዲሱ መሣሪያ የምርት መከታተያውን ሥርዓት የተሻለ ለማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፣
   ለ) በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ውስጥ የሚደረገውን የማስተካከያ ሥራ ባህሪያት፣ እና
   ሐ) በኮምፒውተሮች እና በሌሎች መሣሪያዎች ላይ መሣሪያው የሚገጠምበትን እና የሚሠራበትን ሁኔታ፣
5) የተፈቀደለት ሰው ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ የምርት መስመሮች በሚከተለው አኳኋን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡-
   ሀ) የማይሠሩ መስመሮችን በ24 ሰዓት ውስጥ፣ ወይም

## 28. PRODUCTION ACCOUNTING SYSTEM

1) The Tax Authority may require a manufacturer or importer of excisable goods to facilitate installation of a production accounting system.
2) The production accounting system shall be composed of-
   a) product authentication and validation equipment;
   b) devices for the control, registration, recording and transmission of data on quantities of excisable goods which have been manufactured or imported by the licensee.
3) the production accounting system shall-
   a) be installed on all production lines at the manufacture’s premises corresponding to each packaging machine or labeling machine; and
   b) for the management of imports, be installed in the manner specified by the Tax Authority.
4) Where a new or modified System is required, the Tax Authority shall notify the manufacturers or importers of excisable goods in writing at least thirty days before the installation and integration of the new or modified System and the notice shall state—
   a) The requirements for the equipment to facilitate use of the system;
   b) The adaptive features required, on each production line; and


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ለ) አምራቹ ምርቱን ከ24 ሰዓት በላይ የሚያቋርጥ ከሆነ የምርት ሂደቱ በተቋረጠ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ፣

6) የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለሥልጣን የምርት መስመሮችን መቆጣጠር አለበት፡-

ሀ) የተፈቀደለት ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት የምርት መስመሮች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ መሆኑን ካስታወቀ፣ ወይም

ለ) የምርት መስመሮች የማምረት አቅም ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ፣

7) የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት የምርት መስመሮችን የተቆጣጠረ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት ሰው የታሸገው የምርት መስመር እንዲከፈትለት ለማድረግ አምራቹ ማምረት የሚጀምርበትን ቀንና ሰዓት ጭምር የያዘ የአመራረቱን የጊዜ ሠሌዳ የሚያሳይ ሪፖርት ለታክሱ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

## 29. ትምባሆ እና አልኮልን ስለማጓጓዝ

1) የትምባሆ ቅጠል፣ የተጣራ አልኮል እና የመሳሰሉት ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት በጥሬእቃነት የሚውሉ ትምባሆዎች እና አልኮሎች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ሊጓጓዙ የሚችሉት በተፈቀደለት አከናዋኝ ውክልና በተሰጠው አጓጓዥ ብቻ ነው።
2) ለመጨረሻ ጥቅም የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ከተፈቀደለት አከናዋኝ ወጥተው ወደ ሌላ የተፈቀደለት አከናዋኝ፣ አከፋፋይ፣ ጅምላ ሻጭ ወይም ቸርቻሪ

c) Connectivity features and operating environment for the installation and operation of computers and other equipment

5) A licensee shall report to the Tax Authority any non-operational or inoperative production line-
   a) within twenty-four hours of the production lines becoming non operational ;or
   b) where the licensee does not intend to produce for a period exceeding 24 hours.

6) The Tax Authority may secure the production lines where-
   a) a licensee reports non-operation or inoperative lines under this Article; or
   b) where the installed production capacity of the production lines remains unutilized.
7) Where the Tax Authority secures production lines in accordance with this Directive, the licensee shall provide the Tax Authority with a production schedule indicating the dates and times when the licensee intends to produce to facilitate the unsealing of the production lines.

## 29. TRANSPORTATION OF EXCISABLE TOBACCO AND ALCOHOL GOODS

1) Tobacco and alcohol goods that are usable as raw material for the manufacture of other excisable goods, such as leaf tobacco, undenatured ethyl alcohol, etc. may only be transported by duly certified agents of Licensed Operator.


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሊጓጓዙ የሚችሉት በኤክሳይዝ ታክስ መመሪያ መሰረት ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ምልክት ከተለጠፈባቸው በኋላ ይሆናል።

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ትምባሆ ወይም አልኮል የያዘ ማናቸውም ሰው ከተፈቀደለት አከናዋኝ የማምረቻ ቦታ ወይም ከጉምሩክ መጋዘን አውጥቶ ለማጓጓዝ የሚፈልግ ከሆነ የቃውን ብዛት፤ዋጋ እና ባህሪ ማስታወቅ እና የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ወይም ለታክሱ ክፍያ ተገቢውን ዋስትና ማቅረብ አለበት።

4) ሃላፊነት የተሰጠው የኤክሳይዝ ሰራተኛ በኮምፒውተር በተደገፈ የኦንላይን ስርአት እና/ወይም በአካል በሚደረግ ግንኙነት እቃዎቹ ከስራ ቦታው ወጥተው እንዲጓጓዙ ሊፈቅድ ይችላል። ለመንግስት ገቢ አስበሰብ ሲባል በዚህ አይነት በኤክሳይዝ ሰራተኛ የሚሰጠው ፈቃድ ለመንግስት ገቢ አስባሰብ ሲባል እንደአስፈላጊነቱ በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል።

5) ሀላፊነት የተሰጠው የኤክሳይዝ ሰራተኛ በሚከተሉት ሁኔታዎች የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ እቃዎቹ ከተፈቀደለት አከናዋኝ ወጪ እንዲደረጉ ሊፈቅድ ይችላል፦
   ሀ) እቃው ለውጭ ገበያ እንዲላክ ወደሌላ የጉምሩክ ወደብ የሚጓጓዝ ከሆነ፤ሎጂስቲክስን ለማቀላጠፍ፤
   ለ) እቃው ኢትዮጵያ ውስጥ ወዳለ የቀረጥ ነጻ መደብር የሚላክ ከሆነ፤
   ሐ) የእቃው ብዛት፤ የሚጓጓዥበት ሆኔታ መታየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እቃው የታክሱ ባለስልጣን የዲፕሎማቲክ ወይም ተመሳሳይ መብት ያላቸው ሰዎች ወደሚገለገሉበት ቦታ ነው ብሎ ወደሚወስነው ቦታ የሚጓጓዝ ከሆነ፤

6) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጠው የጉዞ ፈቃድ በእቃው ባለቤት በሚመረጥ፤ ሃላፊነት ሊሰጠው በሚችል እና ከእቃው ጋር አብሮ ለሚጓዝ ሰው የሚሰጥ ይሆናል።ይህ የጉዞ ፈቃድ በዚህ መመሪያ መሰረት በታክሱ ባለስልጣን በጊዜያዊነት የተመደበን የኤክሳይዝ ሰራተኛ ጨምሮ በታክስ ባለስልጣኑ በተመደበ የኤክሳይዝ ሰራተኛ ኢንስፔክት ሊደረግ ይችላል።

2) Finished excisable goods ready for final sale may only be removed to a designated area for transportation to another Licensed Operator ,Wholesaler or Distributor or Retailer only after affixation of designated Excise Markings provided for Excise Stamps Directive.
3) The owner of excisable tobacco and alcohol goods wishing to transport any such goods from excise control from within Licensed Operators manufacturing premises or from a customs warehouse shall report the quantity, value and characteristics of such goods and submit proof of payment of Excise or submission of adequate security for such payment.
4) The designated officer shall, through a computerised online system and/or a physical notice, authorise the removal of the said goods. Such transportation notice may be subject to such conditions which shall be endorsed on the authorisation as the relevant officer may deem necessary for the purpose of safeguarding the revenues of the State.
5) The designated officer may authorise the removal of the goods from the licensed Operator premises without proof of payment of excise in specified circumstances, limited to the following:
   a. To another customs warehouse to facilitate logistics or for export outside Ethiopia
   b. To a duty free shop in Ethiopia
   c. To a location which the Tax Authority has by Notification designated as a beneficiary of diplomatic or other privileges available, subject to conditions regarding quantities, terms of transportation, etc.
6) The issued transportation notice shall be carried by a responsible person, as nominated by the owner of the said goods in the relevant form, who shall accompany the physical shipment. Such transportation notice may be subject to inspection by designated officers of the Tax Authority, including temporary excise


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

officers appointed for these purposes by the Ministry under this Directive.

## ክፍል አራት

## የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ስለማከናወን – በዋጋው በመቶኛ

### 30. የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋምበት ጊዜ

1) ሽያጭ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ከተመረቱበት የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ በወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡

2) ማብራሪያ ወይም ማስረጃ ሊቀርብባቸው ያልቻለ በቆጠራ ጊዜ ያልተገኙ ወይም የጠፉ ዕቃዎች በአዋጁ ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

### 31. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት ስለሚሆን ዋጋ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በዕቃው ዋጋ ላይ ተመስርቶ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረው፡-

ሀ) ለታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ወር ከ30ኛው ቀን በፊት በሚቀጥለው ወር ከፋብሪካው የሚወጡ ዕቃዎች የሚቀርበው ዋጋ ዝርዝር ይሆናል፡፡

ለ) ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ለእያንዳንዱ ምርት ዓይነት፣ መያዣ እና የመያዣ ዓይነት የሚኖረውን ዋጋ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

ሐ) ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው ምርቱን ወደገዥው ለማድረስ የሚወጣውን የትራንስፖርት ሂሳብ የሚጨምር አይሆንም፣

## SECTION IV

## CALCULATING EXCISE: AD VALOREM

### 30. TIMING OF LIABILITY FOR EXCISE TAX

1) Excise Tax becomes due on Excise Goods on removal from the Licensed Factory Premises where the goods were produced, irrespective of whether a sale is made.

2) Excise Tax also becomes due on Excise Goods which cannot be accounted for during a stock take, or where the excise goods are “lost” without any explanation or evidence being provided for the loss.

### 31. PRICE FOR EXCISE CALCULATION

1) Where the excise tax is calculated by reference to the price of the goods this Section must be followed.

2) The price used for each type of excise good must be:

a. The price submitted to MoR on a monthly price list by the 30th of one month covering removals of excise goods in the following month.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

መ) የታክሱ ባለሥልጣን ምርቱ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልበት ወደገበያ መቅረቡን ወይም ታክስ ከፋዩ የገለፀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ "ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ" መሠረት በማድረግ ዋጋውን ይወስናል፡፡

ሠ) በአዋጁ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ትክክለኛ ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚከፈለውን ታክስ የሚወስነው ታክስ ከፋዩ ያስታወቀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች ከሆነ፣ ምርቱ ታክስ ሳይከፈልበት ለገበያ ከቀረበ፣ ወይም ምርቱ ፈቃድ በሌለው ሰው የተመረተ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

ረ) ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረውና ለኤክሳይዝ ታክሰ ክፍያ መሠረት የሚሆነው ሌላ የተፈቀደለት ሰው ለተመሳሳይ ዕቃዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከመያዣው ጋር አብሮ የሚሸጥ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በጠቅላላው ዋጋ ላይ ይሆናል፡፡

ሸ) የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈ.ከልባቸውን የመጨረሻ ምርቶች ለማምረት የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬዕቃዎች የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የሚያዘጋጀው የዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር የእነዚህን ጥሬዕቃዎች ዋጋ የሚጨምር መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የንፁህ አልኮል በሊትር የሚኖረው ዋጋ እና የትምባሆ ቅጠል በኪሎ ግራም የሚኖረው ዋጋ በዝርዝሩ ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

b. A price must be allocated to all brands produced per unit/container size and per container type.

c. The price used for excise purposes will exclude any transportation costs.

d. Where it is found by the Tax Authority that excise goods have entered the market with no excise having been paid, or an under-declared amount of excise being declared, the "Fair Market Value" must be used.

e. The Fair Market Value as defined in Article 3 of the Proclamation will be used in cases where the Tax Authority has identified under-declared excise or on excise goods which have entered the market without any excise being paid, or those excise goods produced by unlicensed producers.

f. The Fair Market Value on which excise is calculated shall be the price charged legitimately by a licensed manufacturer of the relevant goods on similar goods.

g. The cost of returnable bottles returned to the factory and re-used will be calculated and offset from the monthly excise declaration.

h. In circumstances where any excisable raw materials are purchased by the Manufacturer who uses those raw materials in the production of the final


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

product, the Price List must include details of those raw materials at a price per set per litre for ethyl alcohol and per kilogram for tobacco leaf or sugar.

## 32. ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወንበት ዋጋ ግልፅ እንዲሆን እና አምራቾች በእኩል መወዳደር እንዲችሉ እያንዳንዱ የተፈቀደለት ሰው የምርቱን ዋጋ ዝርዝር በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን እና ዓይነት እንዲሁም ለገበያ በሚውልበት ቦታ በመለየት ለታክሱ ባለሥልጣን በየወሩ ማቅረብ አለበት፡፡

2) ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች በተዘጋጀው ማንዋል ውስጥ በዝርዝር ይመለከታል፡፡

3) የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት፣ የነጠላውን መጠን እና ዓይነት የሚያሳየው የዋጋ ዝርዝር የእያንዳንዱን ምርት የማምረቻ ወጪ እና የትርፍ ህዳግ የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡

4) ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የተሸጠ እንደሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው በደረሰኙ ላይ የተመለከተው ዕቃው የተሸጠበት ትክክለኛ ዋጋ ይሆናል፡፡

5) ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ዋጋው ያልተከፈለበት ከሆነ ከፋብሪካው በወጣው ዕቃ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በቀረበው የዋጋ ዝርዝር በተመለከተው ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

6) ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበትን ቀን፣

ለ) የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣

ሐ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ ይህንኑ፣

## 32. MONTHLY PRICE LIST

1) In order for a level playing field and a clear and transparent understanding of the price on which excise is calculated, each Licensed Producer must submit a price list to MoR listing each brand or type of excise good, the container size and type of container or package and providing the price for excise purposes for each product.

2) The manner in which the Monthly Price List must be completed and submitted will be published in an Excise Producer Manual which will be available to all Licensed Excise Producers..

3) The price for each brand, unit size and type of unit must include a detailed break down of the cost of goods for production plus a reasonable mark-up.

4) If the goods are sold at a higher price than that submitted, the excise must be calculated at the higher price which must appear on the invoice showing the first sale from the Licensed Factory.

5) If goods are sold at a lower price, or are removed from a licensed factory premises, without any payment, the price submitted on the price list must be used to calculate the excise on such removals.

6) An invoice and/or delivery note must accompany the goods removed from a licensed Factory showing:


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

መ) ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፣

ረ) የዕቃዎቹን ብዛት፣

ሰ) የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ዋጋ፣

ሸ) ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ፣

7) ከፋብሪካ ወጪ የተደረገው የእያንዳንዱ የምርት አይነት የማስረከቢያ ሰነድ ሊይዝ የሚገባው መረጃ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራቾች ማንዋል ውስጥ ተካቷል።

a. The date of removal;

b. The delivery address of the goods;

c. The customer;

d. If the customer is an affiliated company to the producer then this must be clear;

e. The type of excise goods;

f. The quantity of excise goods;

g. The price for each unit of excise goods;

h. The excise due.

7) The nature of the Delivery Note for each type of removal is contained in the Excise Producer Policy Notice.

## 33. የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ

1) የእያንዳንዱ ወር የኤክሳይዝ ታክስ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ያለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

2) የተፈቀደለት ሰው ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ባለው 30 ቀን ጊዜ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክሱን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

3) ከዋጋ ዝርዝር፣ ከማስረከቢያ ሰነድ እና ከደረሰኝ ጋር ማመሳከር እንዲቻል በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ውስጥ የእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት እና ለሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ሳይሸጥ የተመለሰው ተለይቶ ማስታወቂያ ሊቀርብበት ይገባል፡፡

4) የታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ የታክስ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተውን መረጃ በተፈቀደለት አምራች ከሚያዘው የምርት፣ በመጋዘን የሚገኝ ዕቃ እና የሽያጭ መረጃ ጋር ማመሳከር አለበት፡፡

## 33. EXCISE DECLARATION

1) An excise tax declaration must be submitted to the Tax Authority by the 30th day of the month following that in which the excise declared became due.

2) The Licensed Manufacturer shall pay the excise to the Tax Authority by the 30th day of the month following that in which the excise declared became due.

3) A separate excise declaration, or schedule within the excise declaration, must be submitted for each brand of excise goods returned because of not being sold so that it can be linked to the price list submitted and to the invoices and delivery notes issued on removal from the Factory Premises.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

5) የተፈቀደለት ሰው የታክስ ማስታወቂያውን ትክክለኛነት የሚያስረዱ ደረሰኞችን፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን እና የየዕለቱን የኤክሳይዝ ታክስ መረጃ በሚገባ መያዝ አለበት፡፡

6) የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ መረጃዎችን በሚገባ ያልያዘ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑ በተጨማሪ ካልተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እጥፍ የሆነ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዱን የመሠረዝ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

**34. የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ ዕቃዎች**

1) እያንዳንዱ የተፈቀደለት ሰው በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡፡

2) ከዚህም በተጨማሪ የተፈቀደለት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሀዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡-

ሀ) በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬዕቃና የመጨረሻ ምርት፣

ለ) አዲስ ወደፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን፣

ሐ) በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬዕቃዎችን፣

መ) በፋብሪካው የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን፣

ሠ) በፋብሪካው ተመርተው ወደፋብሪካው መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን

ረ) የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

4) The Tax Authority shall verify all excise declarations in line with production, stock and sales records held by each Licensed Manufacturer.

5) Invoices, Delivery Notes and Daily Excise Accounts mut be kept by all Licensed Manufacturers as evidence that the excise tax declared is accurate.

6) Any failure to provide evidence will result in penalties double the unpaid excise plus other penalties as listed in Article 39 of the Proclamation and the imposition of conditions on a Licensed Manufacturer’s Excise Licence.

**34. STOCK TAKES AND LOSSES**

1) Every Licensed Excise Manufacturer must, at least every six months perform a full stock take of goods, including raw materials of each Licensed Factory Premises.

2) In addition, a rolling monthly stock must be taken which shows:

a. Stock on hand of each raw material and final product on the last day of each month;
b. Raw materials received;
c. Raw materials used in production;
d. Final products received;
e. Final products entered into stock from production;


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሸ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎችን፣

3) የተፈቀደለት ሰው ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

4) የዕቃ መጥፋት ተቀባይነት የሚኖረው የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ሪፖርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል፡፡

5) በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት የታክሱ ባለሥልጣን ይህንኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

6) ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬዕቃዎች

### 35. በተፈቀደለት አምራች የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ

1) የተፈቀደለት ሰው የመጨረሻውን ምርት ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬዕቃዎች ራሱ የሚያመርት እና የኤክሳይዝ ታክሱ ስሌት በዋጋው በመቶኛ በሚሆንበት ጊዜ የጥሬዕቃው ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ነው፡፡

f. Goods leaving the Factory on duty payment;

g. Goods leaving the Factory with no excise due (destructions / exports).

h. Accidental losses must be recorded and reported.

3) Licensed Excise Manufacturers must keep evidence of goods exported.

4) Losses can only be explained where a Loss Record is kept showing the reason for the loss and an investigation into how the loss occurred. In the absence of a Loss Record, then all excise must be paid on the quantity of lost excise goods.

5) The Tax Authority must be notified at least 14 days in advance of a full stock take being carried out at each Licensed Factory.

6) All activities at each factory must be suspended for the duration of the stock take.

## SECTION V

## EXCISABLE RAW MATERIALS

### 35. PRICE USED FOR EXCISABLE RAW MATERIALS PRODUCED IN ETHIOPIA BY THE PRODUCER

1) Where the Licensed Excise Producer grows its own raw materials and excise is chargeable on those raw materials at an ad valorem rate, the price used must be one which is a “Fair Market Value”.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

2) ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው ጥሬዕቃውን ለማምረት የሚወጣው ወጪ እና ጥሬዕቃው ለሦስተኛ ወገን ቢሸጥ የሚታከለውን የትርፍ ህዳግ የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

3) የተፈቀደለት ሰው ጥሬዕቃውን ለሦስተኛ ወገን ጭምር የሚሸጥ ከሆነ፣ ለሦስተኛ ወገን የተሸጠበት ዋጋ የመጨረሻውን ምርት ለሚያመርተው ፋብሪካም ጥሬዕቃው የተሸጠበት ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰነው የእያንዳንዱ ጥሬዕቃ ዋጋ የተፈቀደለት ሰው በሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ መካተት አለበት፡፡

2) A Fair Market Value is at least Cost of Goods plus any mark-up/profit margin as if the goods were being sold to a third party.

3) Where the excisable raw material is also sold to a third party, then the same price as used to sell the goods to the third party must be used to calculate the excise on goods destined for the Factory producing the final product.

4) The price for each type of excisable raw materials must be included in the Monthly Price list submitted under section 9 above.

## ክፍል ስድስት

## <u>በቁርጥ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች የመጠን አወሳሰን</u>

### 36. በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው

1) በመደበኛ ሁኔታ በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሰላው በዕቃው ማሸጊያ ላይ የተመለከተውን ብዛት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማሸጊያው ላይ ከተመለከተው በላይ ሆኖ ከተገኘ፣

ሀ) ዕቃው ውርስ እንዲደረግ፣

ለ) በተጨማሪው ዕቃ ላይ ወዲያውኑ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል፣

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት ቅጣት እንዲጣል፣

ሊወሰን ይችላል፡፡

## SECTION FIVE

## CALCULATING THE VOLUME FOR SPECIFIC EXCISE RATES

### 36. QUANTITY FOR EXCISE

1) Under normal circumstances the labelled quantity will be used to calculate the excise on all goods that are subject to a specific excise rate.

2) Notwithstanding sub article 1 of this article, where it is found that the quantity of excise goods exceeds the labelled quantity:

a. The goods are liable to forfeiture;
b. The extra excise is due to be paid immediately; and
c. Penalties are due under Article 39 of the Proclamation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተጨማሪውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ወይም ቅጣት እንዲጣልበት የሚደረገው አምራቹ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ይዞ የተገኘው ሰው እና አምራቹ በአንድነት እና በነጠላ ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## በአገር ውስጥ ጥሬዕዎች መጠቀምን ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ማስረጃ

### 37. የአገር ውስጥ ጥሬዕቃ ስለመጠቀም

1) በአዋጁ በአገር ውስጥ ጥሬዕቃ ተጠቅመው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርቱ አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ የተፈቀደ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት ሰው ጥሬዕቃው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ እርሻ የተመረተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

2) ጥሬዕቃው በአገር ውስጥ የተመረተ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበው መረጃ የማስረከቢያ ሰነድ፣ ደረሰኝ፣ ከአምራቹ ጋር የተደረገ ውል እንዲሁም የአምራቹን ስም እና አድራሻ ይጨምራል፡፡

3) የተፈቀደለት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልቻለ ከውጭ አገር በሚመጣ ግብዓት ለሚመረቱ የተወሰነው የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የምርት ብዛት ልኬት

### 38. የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት ስለመመዝገብ – ጠቅላላ

1) የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው በዋጋው በመቶኛ ወይም በቁርጥ ወይም በሁለቱም ቢሆንም የተመረተው ምርት ብዛት በትክክል ሊመዘገብ እና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

3) The person liable to pay the extra excise and receive the penalty is the Producer of the goods, or jointly and severally, the person holding the excise goods at the time the offence was found.

## SECTION VII

## MEASUREMENT OF QUANTITY

### 37. MEASURING THE QUANTITY OF EXCISE GOODS PRODUCED: GENERAL

ሦAll excise goods, irrespective of whether the excise is calculated by reference to ad valorem, specific or a combination of both calculation methodologies must be measured and the quantity of stock produced accurately recorded and reported.

1) All equipment used to store and produce excisable goods must be accurate and provide access for measuring equipment to be used to accurately assess the quantity of any type of excise good within the Licensed Factory premises.

2) 3/ If the authorized person fails to provide the evidence listed in Sub-Article 1 of this Article, the applicable tariff rate for products manufactured with imported inputs shall apply.

## SECTION VII

## MEASUREMENT OF QUANTITY

### 38. MEASURING THE QUANTITY OF EXCISE GOODS PRODUCED: GENERAL

1) All excise goods, irrespective of whether the excise is calculated by reference to ad valorem, specific or a combination of both calculation



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

2) በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ወይም ለማከማቸት የሚውሉ መሣሪያዎች ወይም የማምረቻና የማከማቻ ቦታዎች የዕቃዎቹን ብዛት እና ዓይነት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል የመቁጠሪያ መሣሪያ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

## 39. የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት ስለመለካት

1) የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት የሚለካው በሁለት ቁልፍ ደረጃዎች ይሆናል፣ እነዚህም፡-

   ሀ) በምርት ሂደት ውስጥ ፈሳሹ በጥቅል ተከማችቶ በሚገኝበት ጊዜ፣

   ለ) ፈሳሹ በሚታሸግበት ጊዜ፣

2) ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው በጥቅል ተከማችቶ የሚገኘው ፈሳሽ እና የታሸገው ፈሳሽ ብዛት እስከተቻለ ድረስ እኩል መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

3) ፈሳሽ ምርቱን በማሸግ ሂደት የሚባክነው መጠን ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

4/ የተፈቀደለት ሰው የማሸግ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እና ከተከናወነ በኋላ ፈሳሹን የሚለካ አስፈላጊው ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ በፋብሪካው ውስጥ መግጠም እና የመሣሪያውን ንባብ በየጊዜው መወሰድ አለበት፡፡

5) ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው ፈሳሽ የሚለካውን ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ትክክለኛነት በየጊዜው ማስመርመር እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቅበት ጊዜ የምርመራው ውጤት እንዲሰጠው ማድረግ አለበት፡፡

6) ፈሳሽ 10 ሊትር ወይም ከዚያ በታች በሆነ ቆርቆሮ፣ ጠርሙስ ወይም ሌላ አነስተኛ ማሸጊያ በሚታሸግበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የኤክሳይዝ ታክሱ በእያንዳንዱ ማሸጊያ

methodologies must be measured and the quantity of stock produced accurately recorded and reported.

2) All equipment used to store and produce excisable goods must be accurate and provide access for measuring equipment to be used to accurately assess the quantity of any type of excise good within the Licensed Factory premises.

## 39. MEASURING QUANTITY: LIQUIDS

1) For liquids, there will be two key areas of measurement:

   a. During production when the liquid is in bulk form; and

   b. When packaged.

2) For liquids the equipment used by any Licensed Excise Producer must reconcile the bulk liquid and the packaged liquid as accurately as possible.

3) Any losses in the packaging process must be recorded.

4) Flow meters, or other measuring device, must be installed and readings taken of each relevant


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ውስጥ ባለው ፈሳሽ ትክክለኛ መጠን ላይ ተመስርቶ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የተፈቀደለት ሰው የሚጠቀምበት ብዛትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ "የአማካኝ ይዘት" ከሆነ የታሸገው ፈሳሽ አማካኝ ይዘት በቆርቆሮው ወይም በጠርሙሱ ወይም በህትመቱ ወይም በብረት በርሜል ወይም በእንጨት በርሜል የታሸገ በሚሆንበት ጊዜ በደረሰኙ ወይም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ ከተመለከተው ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

8) የአማካኝ ይዘት ዘዴ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በጥቅል የተያዘው ፈሳሽ ልኬት፣ ቀጥሎም የታሸገበት ዕቃ ብዛት፣ የማሸጊያው ልክ በትክክል መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ልኬት ከ2% ያልበለጠ ብክነት ሊኖር እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት የታሸገው ምርት በጥቅል ከተያዘው ፈሳሽ ጋር እኩል መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡

9) እያንዳንዱ የተፈቀደለት ሰው በፈሳሽ ማከማቻው የተያዘው ፈሳሽ ብዛት ወደማሸጊያ ከተላለፈው ብዛት ያልበለጠ መሆኑን ለማረጋገጥ በማሸጊያዎች የመሙላቱ ሂደት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

10) የተፈቀደለት ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ለሚያከናውነው የክትትል ሥራ አጋዥ እንዲሆን በቁጥጥር ሥራው የተገኘውን ውጤት መመዝገብ እና ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተደጋጋሚ ከመጠን በላይ ፈሳሽን የመሙላት ተግባር መከናወኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያለ እንደሆነ የተፈቀደለት ሰው ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

flow meter or similar method before and after all packaging operations.

5) Any equipment used must be calibrated and calibration tables must be readily available to MoR officers on request.

6) When measuring liquid into cans, bottles and other small pack containers with a capacity of 10 litres or less, MoR can require excise tax to be accounted for on the actual quantity of the liquid in each container.

7) Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article , if the licensed producer uses the ‘average system’ of quantity control, the average contents of packages must not be less than the declared contents (the volume marked on the can or bottle or label or, in the case of kegs and casks, on the invoice or delivery note).

8) Where the average contents method is used, measurement of the bulk liquid must be recorded, followed by the quantity of packages and package size which must match the bulk liquid, taking into account a no greater than 2% loss tolerance.

9) Each Licensed Excise Producer must monitor the filling process to make sure that the quantity put into the package does not regularly



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## ክፍል ዘጠኝ

## የአልኮል ጥንካሬን ስለመለካት

**40. የአልኮል ጥንካሬ መለካት - በማብላላት የሚመረት**

1) የአልኮል መጠጦችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የአልኮል ጥንካሬውን መሠረት በማድረግ ከሆነ የእያንዳንዱን ምርት የአልኮል ጥንካሬ መለካት አለባቸው፡፡

2) የተፈቀደለት ሰው የሚገኘው ውጤት ከዚህ በታች በተመለከተው ዘዴ ተለክቶ ከሚገኘው ውጤት ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ የአልኮል ጥንካሬውን ለመለካት ማናቸውንም ዘዴ ለመጠቀም ይችላል፡-

ሀ) ወካይ የሆነ ናሙናን በመውሰድ በተፈቀደው ዘዴ መሠረት ዝቃጭንና ጋዝን በማውጣት የተወሰነ መጠንን በ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት ካልሲየም ሀይድሮክሳይድ ጨምሮ በማጣራት አልካሊን በማውጣት፣

ለ) የማጣራቱ ሥራ ከመከናወኑ በፊት የነበረው መጠን ሳይለወጥ በተጣራ ውሃ በ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ አልኮሉን በመለካት፣

ሐ) በተፈቀደ የፒክኖሜትር ልኬት መሠረት በአየር ውስጥ የሚኖረው ክብደት ከ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ መሆኑን ማረጋገጥ በሚቻል አኳኋን የተጣራው አልኮል ጥንካሬ የተለካ ከሆነ፣

መ) በፀደቀ የአልኮል ላቦራቶሪ ሠንጠረዥ መሠረት የምርቱ የአልኮል ጥንካሬ በተወሰነ መጠን አልኮል በመቶኛ ሲለካ በዚህ ዘዴ የአልኮሉ ክብደት በሠንጠረዡ ከሠፈሩ ሁለት አኃዞች መካከል ከሆነ

excessively exceed the amount declared on the container.

10) These checks should be recorded and provide an adequate audit trail to satisfy the MoR 'due diligence' is being exercised. Where there is evidence of consistent excessive overfilling, additional excise tax will be due.

## SECTION EIGHT

## MEASUREMENT OF ALCOHOLIC STRENGTH

**40. MEASUREMENT OF ALCOHOL STRENGTH: FERMENTED BEVERAGES**

1) Producers of alcoholic beverages to measure the alcohol strength of each product, particularly where the excise rate is defined by the alcohol strength.

2) You may use any method you wish to measure the strength of beer as long as it produces results that agree with those that would be achieved using the reference method which comprises:

(a) taking a representative sample and, after clearing it of sediment and gas in an approved manner, a definite quantity by measure at the temperature of 20°C is made alkaline by the addition of calcium hydroxide, and then distilled;

(b) making up the distillate at the temperature of 20°C with distilled water to the original measure of the quantity before distillation;

(c) ascertaining the strength of the distillate by determining its density in air at the temperature of 20°C by means of an approved pycnometer used in an approved manner;

(d) the strength of product is the percentage of alcohol by volume in an approved



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

የአልኮሉ ጥንካሬ በሊንየር ኢንተርፓሌሽን ይወሰናል፡ ፡

Laboratory Alcohol Table which corresponds to the density determined by this method - where the density falls between 2 consecutive numbers in the table, the strength will be determined by linear interpolation.

## 41. የአልኮል ጥንካሬ መለካት – ከፍተኛ የአልኮል መጠን ያላቸው

1) የአልኮል መጠን መለካት ያለበት በአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ነው፡፡ የሚከተሉት ሁለት መስፈርቶች ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

ሀ) ጥንካሬው መለካት ያለው “በባዶ በሚኖረው ክብደት” ሳይሆን “በአየር ውስጥ በሚኖረው ክብደት” ሲሆን በመጨረሻው “በአየር ውስጥ ወደሚኖረው ክብደት” መለወጥ ይኖርበታል፡፡

ለ) ልኬቱ በሚከናወንበት ጊዜ የፈሳሹ ሙቀት 20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ልኬቱ በተለያየ ሙቀት መከናወን የሌለበት ሆኖ፣ በመጨረሻም ከ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ጋር ተመጣጣኝ ወደሆነ ክብደት መቀየር ይኖርበታል፡፡

2) አውቶማቲክ ዴንሲሜትርን በመጠቀም በትክክለኛ እና በእርግጠኝነት ክብደቱ መለካት አለበት፡፡

3) ከአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ውጪ የሆነ ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ፣ ይህ ዘዴ በኤክሳይዝ ፈቃድ ላይ መመልከት ያለበት ሲሆን፣ ትክክለኛነቱ የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ልዩነት መረጋገጥ አለበት፡

## 41. MEASUREMENT OF ALCOHOL STRENGTH: SPIRITUOUS BEVERAGES

1) Automatic densimeters must measure density. The 2 main criteria are:

(a) the density must be directly measured as ‘density in air’ not ‘density in vacuum’ and then converted to ‘density in air’;

(b) at the time the measurement is taken, the temperature of the liquid must be 20°C - the measurement cannot be taken at a different temperature and converted to the equivalent density at 20°C.

2) The automatic densimeter must carry out density measurements with accuracy and precision.

3) Where a method other than using an automatic densimeter is used, the method must appear on the Licence and be checked regularly for its accuracy by the ta authority.

## ክፍል አሥር

## SECTION NINE



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ስለማውጣት

### 42. ሽያጭ ከተከናወነ በኋላ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ስለማውጣት

1) የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችን ከፋብሪካው እንዲወጣ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡

2) በታወቀ ሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ የወጡ ዕቃዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የማስረከቢያ ሰነድ እና የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥባቸው ይገባል፡፡

3) ወደፊት ሽያጫቸው የሚከናወን ዕቃዎች ካልሆኑ በስተቀር ከፋብሪካ በሽያጭ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት የሽያጭ ደረሰኝ መቆረጥ አለበት፡፡

4) ከተፈቀደለት ፋብሪካ ከወጡ በኋላ የሚሸጡ ዕቃዎች ከፋብሪካው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለደንበኛው ተሸጠው የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥላቸው እና ሽያጩ ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር እንዲጣጣም መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 43. ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ ስለሚወጡ ዕቃዎች

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ሽያጭ የሚከናወነው ከፋብሪካው ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ለሽያጭ እንዲውሉ ከፋብሪካው በሚወጡበት ጊዜ የምርቱን ልዩ መጠሪያ፣ ዓይነት እና ብዛት የሚገልፅ የማስረከቢያ ሰነድ መዘጋጀት አለበት፡፡

2) የማስረከቢያው ሰነድ በታክሱ ባለሥልጣን በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል፡፡

3) ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት፣ ዓይነት፣ ልዩ መጠሪያ፣ ለታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ የተገለፀውን ለኤክሳይዝ ታክስ መሠረት የሆነውን ዋጋ፣ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ልክ እንዲሁም የገኘውን

## REMOVAL OF EXCISE GOODS FROM A LICENSED FACTORY

### 42. REMOVAL WHEN A SALE IS CONFIRMED

1) Excise tax shall be due on all excise goods removed from a licensed factory by the Licensed Producer, when a sale has been confirmed prior to the removal .

2) All removals of excise goods in line with a known sale must be accompanied by a Delivery Note and Invoice as defined in the Directive issued by the Tax Authority.

3) Invoices must be issued at the factory gate, in addition to the delivery note for all removals, except when the removal is for goods which are being removed for a future sale.

4) Invoices for individual sales which are made following the removal of goods from the Licensed Factory Premises must be issued to the customer at the point of sale, and reconciled with the delivery note within 30 days of removal from the factory.

### 43. REMOVAL OF EXCISE GOODS WHERE NO SALE HAS BEEN SECURED.

1) In circumstances where excise goods are removed from a Licensed Factory Premises where no prior sale has been agreed, a Delivery Note must be prepared showing the brand, type and quantity of each excise good removed.

2) The Delivery Note should have the details listed in Excise tax Directive to be issued by the Tax Authority .



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ የሚያሳይ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ገዥ መሰጠት አለበት፡፡

4) የሽያጩ ደረሰኝ ዕቃው ከፋብሪካ በወጣበት ጊዜ የተመዘገበውን የማስረከቢያውን ሰነድ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል፡፡

5) የሽያጭ ደረሰኙ ቅጂዎች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን፣ ዋንኛው ለደንበኛው ይሰጣል፣ ቀሪው ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር ይያያዛል፡፡

6) ከፋብሪካ የወጣውን፣ የተሸጠውን እና ተመላሽ የተደረገውን ዕቃ በትክክል ለማስታረቅ እንዲቻል በሽያጭ ደረሰኙ ላይ የማስረከቢያው ሰነድ ቁጥር እንዲሁም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ የሽያጭ ደረሰኙ ቁጥር መፃፍ አለበት፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## ጌጣጌጥ

### 44. በጌጣጌጥ ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1) የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር እና/ወይም አፓል ወ.ዘ.ተ) በከፊል የያዙ ጌጣጌጦች የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጌጣጌጥነት ያልተሠራ ጥሬ የከበረ ማዕድን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ አፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑት) የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም፡፡

3) When sale is made an invoice shall be completed and issued with each sale which shows the quantity, type and brand of each excise good for each sale, including the price used for excise purposes which was submitted to the Tax Authority, the excise tax payable ,the customer details including TIN and the address of delivery.
4) The invoice must contain details of the Delivery Note number on which the goods were recorded as leaving the Licensed Factory premises.
5) The invoices must be kept in duplicate, with the original invoice being given to the customer, and the copy attached to the delivery note.
6) The delivery note number must be shown on the invoice , and consequently each invoice number must be shown on the Delivery Note so that a full reconciliation can be carried out of the goods removed, the goods sold and the goods returned to the Factory.

## SECTION TEN

## JEWELLERY

### 44. EXCISE TAX ON JEWELLERY

1) Excise tax is payable on all jewellery, part or all of which consists of precious metals (Diamond, Gold, Silver etc).
2) Notwithstanding sub-article 1 of this Article, in its raw state, and prior to being made into the


Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

3) በጌጣጌጥ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ጌጣጌጡ እንደተመረተ ይቋቋማል፡፡

4) ለጌጣጌጥ አምራቾች ጥሬው የከበረ ማዕድን እንደጥሬዕቃ ይቆጠራል፡፡

5) የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ኦፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ) የሚያመርቱ የማዕድን ኩባንያዎች ለኤክሳይዝ ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የለባቸውም፡፡

6) ጌጣጌጥ የሚያመርቱ ድርጅቶች ያመረቱትን ጌጣጌጥ የሸጡበትን የማስረከቢያ እና የሽያጭ ሰነድ መያዝ አለባቸው፡፡

7) የጌጣጌጥ አምራቾች በተፈቀደለት አምራችነት የመመዝገብ እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡

### ክፍል አስራ ሁለት
### ጨው

### 45. በጨው ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1) ጨው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ ጨው ወደአገር የሚያስገባ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያመርት ሰው ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት እና ለተለየ ዓላማ እንዲውል ለማድረግ በፋብሪካ የሚመረት ጨው በድጋሚ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም፡፡

### 46. የተሻሩ መመሪያዎች

የገንዘብ ሚኒስቴር የኤክሳይዝ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 251/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

jewellery, the precious metal is not liable to excise tax.

3) Excise tax becomes due on jewellery at the time when the final jewellery is produced.
4) For manufacturers of jewellery, any precious metal ( diamond, gold, silver, opal etc ) must be treated like any excise raw material.
5) Mines from where the precious metals (diamonds, gold silver are discovered are exempt from excise licensing requirements.
6) Jewelery manufacturers shall keep, delivery notes and invoices showing the destination of the jewellery they produced.
7) All producers of jewellery items must be licensed as Excise Producers and keep all relevant records.

### SECTION TEN
### SALT

### 45. LIABILITY TO EXCISE

1) Salt is liable to excise tax and must be accounted for on import into Ethiopia or on removal from premises where salt is produced in Ethiopia.
2) The excise tax due on salt which is iodized at a Licensed Excise Factory is not subject to secondary excise tax.

### 46. Repealed Directives

The Ministry of Finance Excise Implementation Directive No 251/2020 is repealed and replaced by this directive.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## 47. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገንዘብ ሚኒስቴር የድረ-ገጽ አድራሻ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ፣ ግንቦት 18 ቀን 2017 ዓ.ም.*
*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

## 47. EFFECTIVE DATE

This Directive shall enter into force as of the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the official website of the Ministry of Finance.

Done at Addis Ababa, this 26th day of May 2025

Ahmed Shide

Minister of Finance



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.